ዝናም ዘነመ፤ ጎርፍም ጎረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤
ያንን ቤት ገፋት፤ ነገር ግን አልወደቀም፤
በዐለት ላይ ተመሥርቷልና።
ማቴ ፯፥፳፭

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፩ አጫጭር ዜናዎች

፬ ርእሰ አንቀጽ

፯ ሪፖርታዥ

፱ ቤት አብርሃም

፲፩ ቃለ መጠይቅ

፲፮ የሕፃናት ዓምድ

፲፰ ትዝብት

፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በየወሩ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
Simatsidk12@gmail.com

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# የአርመንያው ፓትርያርክ የእስራኤልን መንግሥት አሳሰቡ

**በካሣሁን ለምለሙ**



*የአርመንያው ፓትርያርክና የእስራኤሉ ፕሬዚዳንት*

የአርመንያው ፓትርያርክ በኢየሩሳሌም ኖሩህን ማኖልያን ለእስራኤሉ ፕሬዚዳንት ሚስተር ሪውቩን ሪቪሊን በጻፉላቸው ደብዳቤ የአርመን ግዛት በሆነችው ኖጎሮን ካራባክህ የአዘርባጃን መንግሥት እስራኤል ሠራሽ በሆኑ የጦር መሣሪያዎች ታግዞ ንጹሐን ዜጎችን እያጠቃ መሆኑን ማስታወቃቸውን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል።

በአዘርባጃንና በአርመን ጦር ሠራዊት መካከል እየተካሄደ ባለው ጦርነት በድንበር አካባቢ የሚኖሩ ንጹሓን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለከፍተኛ ጥቃት እየተጋለጡ እንደሆነ ቅዱስ ፓትርያርኩ በደብዳቤው አንሥተው የአዘርባጃን ሠራዊት በወሰደው የኃይል ርምጃ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንጹሐን ዜጎችና ወታደሮች የተገደሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለከፋተኛ የአካል ጉዳት ተዳርገዋል ብለዋል።

የአዘርባጃን ጦር ሰራዊት በንጹሓን ላይ የወሰደው የኃይል ርምጃ እስራኤል ሠራሽ የሆኑ አውሮፕላኖችንና ድሮኖችን ተጠቅሞ መሆኑን በእስራኤል ብሔራዊ መገናኛ ብዙኃን በድንገት ሲነገር መስማት ያሳዝናል ሲሉ ቅዱስነታቸው ተናግረው፤ የአዘርባጃን መንግሥት የተጠቀማቸው ጦር መሣሪያዎች ሁሉ ከእስራኤል የተላኩና በናጎሮ ካራባክ የሚገኙ ንጹሐንን ለሞትና ለአካል ጉዳት እየዳረጋቸው ነው ሲሉ ፓትርያርኩ ለፕሬዝደንቱ በጻፉት ደብዳቤ ቅሬታ አቅርበዋል፡

ቅዱስ ፓትርያርኩ አያይዘውም እስራኤል ሰላም ወዳድ ሀገር መሆኗ ቢታወቅም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ፀረ ሰላም ከሆነችው አዘርባጃን ጎን መቆሟ ጦርነቱ በአዘርባጃን የበላይነት እንዲጠናቀቅ ከመፈለግ ውጭ በሀገሪቱ መካከል ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ፍላጎት ያላት አይመስለኝም ብለዋል።

እስራኤል ለአዘርባጃን መንግሥት የምታደርገውን የመሣሪያ ድጋፍ ከዚህ በኋላ እንድታቆም ቅዱስ ፓትርያርኩ ጠይቀው እስራኤል የሰላምን ዋጋ ከማንም በላይ ጠንቅቃ የምታውቅና ስቃይን በቅጡ የምትረዳ ሀገር ናት ሲሉም ተናግረዋል።

በመጨረሻም ለአርመንያ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላት ለሆነው የአዘርባጃን መንግሥት የሚደረገው የመሣሪያ ድጋፍ በናጎሮ ኮራባክ በሚኖሩ ንጹሐን ላይ ሞት ማወጅ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ሲሉ ያስረዱት ቅዱስ ፓትርያርኩ የእስራኤሉ ፕሬዝደን ጉዳዩን በደንብ በማጤን ለቅሬታው አስቸኳይ ምላሽ እንደሚሰጡ ተስፋ አደርጋለሁ ሲሉም ተናግረዋል።

የአርመንያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የኦርንታል ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት አባል ስትሆን በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በርሳሲድ ገዥ ንጉስ ተሪዳተስ ሦስተኛ አማካይነት ክርስቲያናዊ መንግስትን የመሠረተች ብቸኛዋ ሀገር ናት እንዲሁም ኖጎሮን ካራባክህ የተባለችው ሀገር ደግሞ በአዘርባጃን ግዛት የምትገኝና በአብዛኛው የአርመንያ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የሚኖሩባት እራስ ገዝ ሀገር መሆኑ ይታወሳል።

# በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቴሌቭዥን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳውያን ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል የተመለከተ ውይይት ተካሄደ

በካሣሁን ለምለሙ




በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ ውይይት ሲካሄድ

ኤስኤኤቲ በተሰኘው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል የተመለከተ ውይይት መካሄዱን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል፡፡

የፓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሶሳይቲ ድርጅት ዋና ጸሐፊ ሚስተር ጆርጅ አሌክሳንደር በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች በንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል በሚያሳይ ዘጋቢ ፊልም አማካይነት ለሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያሪክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል፣ ለሩሲያ ሕዝብና ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ያደረጉትን ጥሪ ተከትሎ የተካሄደ ውይይት መሆኑን ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ቀደም በዋና ጸሐፊው በኩል የቀረበላትን ጥሪ በአዎንታ የተመለከተችው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ‹‹በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ እተፈጸመ ያለ የታቀደ ጥቃት›› በሚል ርዕስ ተጋባዥ ኢትዮጵያውያን እንግዶች፤ ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁ የሩሲያ ቤተክርስቲያን ጋዜጠኞችና የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ተጠሪ በተገኙበት በኤስኤኤቲ በተባለው የቴሌቭዥን ጣቢያዋ ላይ ውይይት እንዲካሄድ ማድረጓን ዘገባው አስታውሷል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀልን ጨምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን ጉዳይ እየተከታተሉ ለፓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሶሳይቲ ድርጅት ሪፖርት ለሚያደርጉት ዲያቆን ሰሎሞን ክብርያና አቶ ምንተስኖት ደስታ በውይይቱ ምስጋና እንደቀረበላቸው ዘገባው አስረድቷል፡፡

ፓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሶሳይቲ የተባለው ድርጅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳውያንን ሰቆቃ ለሩሲያ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት እንዲሁም ለዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ያቀረበ ብቸኛው ድርጅት እንዳደረገው ዘገባው አስታውቆ “ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳውያን ላይ የተፈጸሙ አሰቃቂ የዘር ማጥፋት የወንጀሎችን እየተከታተለ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አሳውቋል” ብሏል፡፡

የፓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሶሳይቲ ዋና ጸሐፊ ሚስተር ጆርጅ አሌክሳንደር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳውያን ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል የተመለከቱ ሪፖርቶችን ለተባበሩት መንግሥታት፣ ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ለዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች እንዳስገቡ ከዘገባው ለመዳት ተችሏል፡፡

# መስቀሉን ዳግም መቅበር አይቻልም!



በመሰደዳቸው ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ የሚያውቀው ሰው አልነበረም። የአይሁድ አላማም ይህ ነበረ ነገረ ድኅነቱ እንዲረሳ ከሰው ልብ እንዲወጣ ማድረግ። ለዚያም ነው ቅድስት ዕሌኒ መስቀሉን ፍለጋ ወደ ኢየሩሳሌም ስትመጣ ኪርያኮስ የተባለ በዕድሜ የገፋ የጥንቱን የሚያውቅ ሰው ያስፈለጋት።

ክርስቶስን በመስቀል ከዚያም መስቀሉን በመቅበር የተጀመረው ፀረ ክርስትና እንቅስቃሴ ቀጥሎ ክርስቲያኖችን እና መምህራኑን በማሳደድ ክርስትናን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ብዙ ርቀት ተጉዟል።

ለ፫፻፴ ዓመታት ያህል በአይሁድ ክፋት እና ጭካኔ ተቀብሮ ተራራ የሚያህል ቆሻሻ የተደፋበት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክበቡር መስቀል በንግሥት ዕሌኒ

አማካኝነት ከተቀበረበት ወጥቶ በከበረው ስፍራ እንዲቀመጥ ከተደረገ እነሆ ፲፯ ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል። አይሁድ ሙት ያስነሣ፣ ድውይ ይፈውስ የነበረውን ክቡር መስቀል ከኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ወስደው ሲቀብሩ ፈዋሽነቱ እንዳይነገር፣ አዳኝነቱ እንዳይመሰከር፣ ታሪኩ ተቀብሮ እንዲቀር አስበው እና አልመው ነበር። መስቀሉን በጊዜው ቆፍረው ማውጣት ያልቻሉ በአካባቢው የነበሩ ክርስቲያኖች ቦታውን ለይተው ቢያውቁም በ፸ ዓመተ ምሕረት በጥጦስ ወረራ ኢየሩሳሌም ስትጠፋ ከሀገር

አይሁድ፣ አላውያን ነገሥታት፣ በየጊዜው የሚነሱ መናፍቃን ባጠቃላይ የእምነቱ ጠላቶች የመስቀሉ የድኅነት ታሪክ እንዳይነገር፣ ፈዋሽነቱ እንዳይዘከር፣ ለዓለም ይዞት የመጣው የመንግሥተ ሰማያት ጥሪ እንዳይመሰከር ያልፈነቀሉት ድንጋይ ያልቆፈሩት ጉድጓድ የለም። በዚህ ሁሉ ውስጥ መስቀልን መድኃኒቷ እና አርማዋ አድርጋ የተነሳቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት መከራን ስትቀምስ ኖራለች።

ብዙ ክርስቲያኖች በየዘመናቱ በተነሱ ዓላውያን (ከግለሰብ እስከ መንግስታት) መብታቸው ሲገፈፍ፣ በነፃነት እንዳያመልኩ ሲደረግ፣ በእምነታቸው ምክንያት ሲገለሉ፣ ሲሰደዱ እና ሲገደሉ ኖረዋል። ሐዋርያት በክርስቶስ ስም እንዳያስተምሩ ተገርፈዋል፣ በካህናተ ጣኦታት የሚመሩ ዓላውያን ነገሥታት ክርስቲያኖቹን ላቆሙት ጣዖት እንዲሰግዱ ካልሰገዱ ዳግም ሀገሩን ለቀው እንዲሰደዱ

ተደርገዋል፡፡ ይህ በዓላዊው ንጉሥ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን በክርስትና እና በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው የመብት ገፈፋ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የክርስቲያኖችን ልዩ ልዩ መብት እንዲከበርላቸው አዋጁን በአዋጅ እስከሻረበት ጊዜ ድረስ በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያኖች በሀገራቸው እንደዜጋ እንዳይቆጠሩ፣ እርስ በርስ እንዳይገናኙ ፣ ንብረታቸው እንዲወረስ፣ በመንግሥት መስሪያ ቤት እንዳይቀጠሩ የመማሪያ ቅዱሳት መጽሕፎቻቸው እንዲቃጠሉ ትዕዛዝ ተላልፎባቸው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈችው በዚያ የጨለማ ዘመን በምድር ላይ መኖርን ተነፍገው በግበብ ምድር እንዲኖሩ የተፈረደባቸው ልጆቿ መከራውን ተሰቅቀው ወንጌልን ከማስፋፋት፣ በክርስትናቸው ከመጽናት አላፈገፈጉም ይልቁንም በጽናታቸው ብዙዎችን የወንጌል ምርኮኛ እስኪያደርጉ ድረስ ክርስትና ለዓለም እንዲደርስ፣ ጨለማው ዓለም እንዲበራ መስቀልን ምርኩዛቸው አድርገው እስከ ምድር ጫፍ ተጉዘዋል፡፡ በወገኖቻቸው ላይ በደረሰው አሰቃቂ ሞት ተሳቀው እምነታቸውን ርግፍ አድርገው ይተዋሉ ሲባል በተቃራኒው ሞትን ተጋፍጠው የክርስትናውን አሸናፊነት አረጋግጠዋል፡፡ ኃላፊያትን ሊተኩ ሌሎች የሃይማኖት ጀግኖች ከሥር እንደ አሸን እየፈሉ በክርስትናው ስብከት እስከ ምድር ዳርቻ ደርሰዋል፡፡

ለመስቀል ጠላት ሆነው የሚነሱ በየጊዜው ቢኖሩም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መስቀልን በጉልላቷ ላይ ተክላ፣ በንዋየ ቅዱሳቷ አትማ በቅጽሯ ሳይቀር ተጎናጽፋው ኖራለች፡፡ በዘመናት ውስጥ መልኩን እየቀያየረ በሚነሣው ፀረ ክርስትና እንቅስቃሴ ውስጥ ልጆቿ በእጃቸው፣ በአንገታቸው፣ በልብሳቸው ሳይቀር መስቀሉን አኑረው ይህ ነው እምነታችን ብለዋል፡፡ ከምኩራበ አይሁድ የተነሣው ጥላቻ ሁለት ሺህ ዘመን ዘልቆ ክርስትና ብዙ እንዳይነገር ከማድረጉም ባሻገር በክርስቲያኖች ላይ ታላቅ መከራና ስደትን አስከትሏል፡፡ መስቀልን ጨምሮ ታላላቅ የክርስትና መገለጫዎችን ለማጥፋት ቢሞክርም ከበረሃው መኻል እየለመለመ፣ ከጭንጫው እየፈለቀ ፣ እየበዛ እዚህ ደርሷል፡፡

ይሁን እንጂ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በዮዲት ጉዲት ብዙዎቹን ልጆችዋን፣ ድንቅ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍቷንና ንዋየ ቅድሳቷን እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናቷን እንድታጣ ተደርጋለች፡፡ በግራኝ አህመድ ወረራ በጨለማ ውስጥ እንድትኳዝ ተገዳለች፡፡ በንጉሥ ሱስንዮስ ዘመን ከምእመናን አልፎ ቀዳሽ ናዛዥ ካህናቷን ተነጥቃለች፡፡ በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ እያለፈች ግን የየእለቱን መንፈሳዊ አገልግሎት ስትሰጥ ኖራለች፡፡ ታላላቆች በመከራው ውስጥ ይወለዳሉና ልጆቿ በሰማዕትነት ሲያልፉ ከሥር ሌሎች ሰማዕታት እየተነሡ እዚህ አድርሰዋታል፡፡ በቅዱሳን ደም የለመለሙ ልጆች አሉዋትና የክርስትናን ሥር ማድረቅ አልተቻለም፡፡

**የክርስትና ሕይወት የመስቀል ጉዞ ነውና በመከራ ውስጥ ማለፍ የግድ ነው፡፡ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በነበራት መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ በልጆቿ መሥዋዕትነት እዚህ ደርሳለች፡፡ እውነት ነው ክርስትና እዚህ ዘመን ላይ እንዲደርስ ብዙ ቅዱሳን በእሳት ውስጥ አልፈዋል፣ በመጋዝ ተሰንጥቀዋል፣ ለአውሬ ተጥለዋል፣ በመንኰራኲር ተፈጭተዋል ፣ እነሱ በሥጋቸው ነደው እያለቁ ክርስትናው እንዲቀጥል ለሌሎች ብርሃን ሆነው አልፈዋል፡፡**

ዛሬም እንደ ዳክሲዮስ ዘመን የቤተ ክርስቲያኒቱን ልጆች ማሳደድና መግደል፣ በግድ እምነት እንዲቀይሩ ማድረግ፣ በገዛ ሀገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲታዩ ጫና ማሳደር እንዲሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማቃጠልና መዝረፍ በዚህ ሁሉ መከራ እንድትጠፋ ማድረግ ትላንት የነበረና ያልተሳካ ነገም የማይሳካ መሆኑን በክርስቶሰ ደም የተዋጁት ልጆቿ መሥዋዕትነት ከፍለው አሳይተውናል። አይሁድ ክርስቶስ የተሰቀለበትን ክቡር መስቀል አርቀው ቀብረው ለዘመናት ቆሻሻ በመድፋት እንዲረሳ ጥረት እንዳደረጉት ሁሉ ዛሬም መስቀሉን ከጉልላቷ ላይ አውርደው ቤተ ክርስቲያንን በማቃጠል እዚያ ቦታ ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረ ለማድረግ በዕቅድ ረጅም መንገድ ተሄዷል። ክርስቲያኖችን በመግደል፣ በማረድ እና ከቀዬአቸው እንዲሰደዱ በማድረግ እዚያ ቦታ ያለው የክርስቲያኖች እና የክርስትና ታሪክ እንዲረሳ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ተደርጓል፤ ሆኖም "ዲያቢሎስ ዝናሩን ጨረሰ ቤተ ክርስቲያንን ግን አልጎዳትም" እንዳለ ሊቁ መስቀሉን የመቅበር አላማው አልተሳካም።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ በተነሡ ሰማዕታት ጠፋች ሲባል እየበዛች በወንጌል የምድርን ዳር እያዳረሰች፣ ወደቀች ሲባል ጸንታ እየቆመች፣ አበቃላት ሲባል በአዲስ ጉልበት እንደገና እየጀመረች እዚህ ደርሳለች። በቅርቡ በሊቢያ ማኅተመ ክርስትናችን የሆነውን የአንገታችንን ክር አንበጥስም ብለው የተሠዉ ወንድሞቻችን በክርስትናችን እንድንጸና በሰማዕትነት ጽናታቸው አርአያ ሆነውናል። ዛሬም ስለ ክርስትናቸው ዋጋ የከፈሉ ክርስቲያን ወገኖቻችን ቤተ ክርቲስያን እንድትቀጥል ክርስትናም እንዲስፋፋ፣ ሰማዕት ሆነዋል። እየሞቱ ፀንተዋል፣ በጠፉ ቁጥር በዝተዋል ዓለም ያልተረዳው ይህን ታላቅ ምሥጢር ነው። ቤት ንብረት በማሳጣት ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም የሀብት መስፈርት ብቻ ምንም ነገር እንዳይኖራቸው ማድረግ ይቻል ይሆናል ሰማያዊ የሆነውንና የክርስትና ሀብታቸውን መንጠቅ ግን አይቻልም። እየሞቱ መኖር እየተሰደዱ መስፋት፣ እየጠፉ መብዛት የነበረ፣ ያለና የሚኖር ነው። ከጥንት ጀምሮ የክርስትና ጉዞ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው።

በዘመናት መሐል እንዲረሳ ለማጥፋት በተረባረቡበት መጠን ድንጋይ እንደተጫነው ተክል በየአቅጣጫው እያፈተለከ፣ በተገኘው አቅጣጫ ሁሉ ክርስትና ተስፋፍቷል። ቃሉን ማሰር አይቻልምና። በጠንካራ መዳፍ ሊጨፈለቅ ቢሞከርም እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት አድጎ ትልቅ ዛፍ ሆኗል። እውነቱ ይህ ነው በመከራ ውስጥም ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ለሰከንድ ቆሞ አያውቅም። ሁልጊዜ ቢሆን ክርስትናን መልሶ ለመቅበር የሚደረገው ትግል ከንቱ የሚሆነው ለዚህ ነው በተራራ ላይ ያለች ከተማን መሠወር አይቻልምና።

በርግጥ የክርስትና ሕይወት የመስቀል ጉዞ ነውና በመከራ ውስጥ ማለፍ የግድ ነው። በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በነበራት መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ በልጆቿ መሥዋዕትነት እዚህ ደርሳለች። እውነት ነው ክርስትና እዚህ ዘመን ላይ እንዲደርስ ብዙ ቅዱሳን በእሳት ውስጥ አልፈዋል፣ በመጋዝ ተሰንጥቀዋል፣ ለአውሬ ተጥለዋል፣ በመንኰራኲር ተፈጭተዋል ፣ እነሱ በሥጋቸው ነደው እያለቁ ክርስትናው እንዲቀጥል ለሌሎች ብርሃን ሆነው አልፈዋል። በዚህ ታላቅ ገድል ውስጥ አልፎ የመጣውን ክርስትና ነው ዛሬም ብዙዎች ልክ እንደ መስቀሉ ሊቀብሩትና ሊያዳፍኑት የሚሞክሩት። በስደት ውስጥ ያለፈውን ክርስትና ነው ዛሬም በስደት እንዲጠፋ የሚጥሩት። በቅብብሎሽ እዚህ የደረሰውን ክርስትና ነው አማኙን በመግደል ሊያጠፉት የሚታትሩት። አዎን እንደ አይሁድ ዘመን በቅንአት ተነሣሥቶ ክርስቲያኖችን መግደል ማሳደድ፣ መስቀሉን ከጉልላቷ ላይ ማንሳት ይቻል ይሆናል መልሶ መቅበር ግን አይቻልም። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን በመከራ ደምቃ ፣ በመስቀል ከፍ ብላ ለእኛ ለክርስቲያኖች ለዘለዓለም ስታበራልን ትኖራለችና።

*ወስብሐት ለእግዚአብሐር!*

# ''አንገቱ ላይ ማዕተብ ያሰረ ኦሮሞ አናውቅም''

**በካሣሁን ለምለሙ**

**ክፍል ሁለት**

*የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትም ደግሞ ክፍል ሁለትና የመጨረሻውን ክፍል ይዘንላችሁ ቀርበናል። መልካም ንባብ።*

የኦሮሚያ ፖሊስም ሕይወት ከማዳን ይልቅ በንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ላይ ቀጥታ ጥይት በመተኮስ ለአክራሪው ቡድን ከለላ ሰጥቷል፤ የመሣሪያና የስንቅ ትጥቅ ድጋፍም አድርጓል። ሕግን እንዲያስከብር ጥሪ ሲደረግለት "ትዕዛዝ አልተሰጠኝም" በማለት የሰው ሕይወት ሲጠፋ በታዛቢነት ተመልክቷል። እነዚያ ግፍ የተፈጸመባቸው ምእመናን በአሁኑ ሰዓት በሕይወት የተረፉት በሕክምና ቦታ፣ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በፖሊስ ጣቢያ ተጠልለው ይገኛሉ። ጥቃቱ የተፈጸመባቸው አንዳንድ ምእመናን እንደሚናገሩት ከሆነ የተፈጸመው ጥቃት የተቀናጀና በግልፅ የመንግሥት የፀጥታ አካላትም ተሳትፎ ያደረጉበት ነበር። በአክራሪ ኃይሉ የተፈጸመው ጥቃት ሙሉ በሙሉ ሃይማኖት ተኮር ሲሆን በኦርቶዶክሳውያኑ ላይ ሆን ተብሎ ታቅዶና ታስቦ የተፈጸመ እንደሆነ ብዙ ማሳያዎች እንዳሉ በዝርዝር ተናግረዋል።

የዞን አስተዳዳሪዎች፣ የፀጥታ ኃይሎችና የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች ባሉበት መፈጸሙ ደግሞ ጥቃቱ ቀደሞ የታቀደ እንደሆነ አመላካች ነው በማለት ምዕመናኑ ያክላሉ። የደረሰው ጥፋት ከመፈጸሙ በፊት መከላከልም ሆነ መቀነስ ይቻል እንደነበር የገለጡት ምእመናኑ ነገር ግን የመንግሥት መዋቅሩ የተሳተፈበት በመሆኑ በሕይወታችንና በንብረታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብናል ይላሉ። አንዳንድ የ ፀጥታ ኃይሎች ሁሉም ነገር ከወደመ በኋላ ለይስሙላ ጥፋቱን ለመከላከል ጥረት እያደርጉ እንደነበረ የተናገሩም አልጠፉም።

በሻሸመኔ ከተማ ብቻ እስካሁን ደረስ ከ100 በላይ የኦርቶዶክሳውያን የንግድ ተቋማት ወድመዋል። ጉዳት ከደረሰም በኋላ ምእመናኑ ያለምንም አጋዥ እርስ በእርሳቸው ብቻ እየተደጋገፉ ይገኛሉ። በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተጠልለው ለሚገኙ ምእመናን ደግሞ የአካባቢው ምእመናን አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረጉላቸው ይገኛሉ። የሐዋሳ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ ሌሎች ከተሞችም የርዳታ እጃቸውን እየዘረጉ ይገኛሉ። የአካባቢው የመንግሥት አካልም ምእመናንን ለተጨማሪ ጥቃት ከማመቻቸት ውጭ የሕግ ከለላም ሆነ ማኅበራዊ ድጋፍ እያደረገላቸው አይደለም። ንብረታቸውም ሆነ ሕይወታቸው የተረፈ ምእመናን አሁንም ድረስ በከፍተኛ የፀጥታ ሥጋት ውስጥ ይገኛሉ። አንዳንዴም አክራሪ ቡድኑ ‹‹ገንዘብ ካላመጣችሁ ቤታችሁንና ንብረታችሁን እናቃጥላለን፤ እንዘርፋለን›› በማለት ምእመናኑ ላይ ከፍተኛ ዛቻና ማስፈራሪያ እያደረሰባቸው እንደሆነ ከምእመናኑ እየወጡ ያሉ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህንን የፈሩ በርካታ ምእመናን ቤት ንብረታቸውን ጥለው ወደ አጎራባች ክልሎች ተሰደዋል።

ጥፋት ያደረሰ አክራሪ ጽንፈኛ ቡድንም ሆነ በግብረ አብርነት ሲያገለግሉ የነበሩት የፀጥታ ኃይልና ሌሎች የመንግሥት አካላት ተይዘው ለፍርድ እየቀረቡ ነው የሚል ሀሳብ ቢኖርም የአካባቢው የፀጥታ ኃይል ለአክራሪ ኢስላማዊ ጽንፈኛ ኃይል በመወገኑ በፀጥታ ኃይሉ ምንም ዓይነት እምነት እንደሌላቸውና ራሳቸውንና ንብረታቸውን ከጥቃት ለመከላከል አደረጃጀት እየፈጠሩ እንደሆነ ምዕመናኑ ያስረደሉ።

በኦርቶዶክሳውያን ሕይወትና ንብረት ላይ እየደረሰ ያለው እልቂት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እየተፈጸመ ያለው ሕዝበ ሙስሊሙ በሚበዛባቸው አካባቢዎች እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው። ይህ ድርጊት የሚፈጸመው በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ቢሆንም በተደጋጋሚ እየተከሠተ ያለው ግን በኦሮሚያ ክልል ነው። ይህ ደግሞ እስላማዊ አክራሪ ጽንፈኛ ቡድኑ ለዘመናት ሲያልመው የነበረውን ከኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የፀዳ ክልልና ሀገር ለመመሥረት ያለውን የቀን ቅዠት ሕልሙን ዕውን ለማድረግ እያደረገው ያለውን ጥረት የማያሳይ ነው። ይህንን ለማሳካት ደግሞ ተለያዩ ሥልታዊ እቅዶችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በነደፈው ሥልታዊ ዕቅድ መሠረት በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናንና በንብረታቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርስ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ

ደግሞ የሚጠቀመውን ስልት በመለዋወጥ ላይ ይገኛል:: ቀደም ሲል በተናጠል ክርስቲያኖችን እያሳደደ ሲያርድ፤ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥል እንዲሁም ማዕተብ ሲያሥበጥስ አስገድዶ ሲያሰልም ነበረ::

የሰሞኑን ደግሞ ጽንፈኛ ቡድኑ ስልቱን ቀይሮ ምእመናኑን በአሠቃቂ ሁኔታ ከመግደል እንዲሁም በኢኮኖሚ እንዲጎዱና ተስፋ ቆርጠው አካባቢውን ጥለው እንዲሄዱ ከትንንሽ የንግድ ተቋማት ጀምሮ ትልልቅ ተቋማትን እያወደመ ይገኛል:: ይህ የሚሆነው ምእመናኑ የሚበሉትና የሚጠለሉበት ቤት ከሌላቸው ተማሪው ሀገሩን ጥለው ይሄዳሉ በሚል እሳቤ ነው:: ይህ ከተሳካ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ያለ ምእመናን ባዶ ናትና እስላማዊው ጽንፈኛ ቡድን ቤተ ክርስቲያንና ሀገርን ለመቆጣጠር መንገድ ይጠርግለታል:: ስለሆነም በዚህ ወቅት በኦርቶዶክሳውያን ላይ እየተፈጸመ ያለው ደባና ሴራ በቀላል ሊታይ የሚገባው አይደለም:: ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ሊነቃና ሕይወቱንና ንብረቱ ሊታደግ ይገባል:: የምእመናንን ደኅንነት በመጠበቁ ረገድም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው::

መንግሥት በራሱ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች መኖሩን ቢያውቅም ለቤተ ክርስቲያን ያለው ትኩረት አናሳ መሆኑን ነው እስከ አሁን ድረስ በሀገሪቱ ውስጥ እየተካሔዱ ያሉ ነገሮች በተጨባጭ የሚያሳዩት:: የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የመንግሥት ኃላፊዎችን ጨምሮ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች በእስላማዊ ጽንፈኛ ቡድን የተጠለፉ በመሆናቸው ነው:: በመሆኑም እስላማዊው ጽንፈኛ ቡድን ወንጀል በሚፈጽምበት ወቅት ከፍተኛ ሽፋን ሲሰጥ ተስተውሏል ፤ የምእመናንን ሞት እንዳላየ ታልፏል:: አለፍ ሲልም ንጹሓን ኦርቶዶክሳውያንን በጥይት ይገደላሉ:: መንግሥት ያለፈውን የኦርቶዶክሳውያንን ሥቃይ በትምህርትነት በመውሰድ በክርስቲያኖች ላይ ጭካኔ የተሞላበትን ጭፍጨፋ የሚፈጽሙ አክራሪዎች ላይ በማያዳግም ሁኔታ የሕግ የበላይነትን ሊያረጋግጥ፣ ለተጎዱ ምእመናንም በጉዳታቸው ልክ ተመጣጣኝ ካሳ ሊሰጣቸ፣ ከዚኽ በተጨማሪም መንግሥት ወንጀልን ቀድሞ የመከላከል አቅሙን ሊያጎለብት ይገባዋል::

ከቤተ ክርስቲያን አንጻር ስንመለከት ደግሞ ምእመናንና ንብረታቸውን ከጥቃት ለመከላከል ምንም የተሠራ ሥራ እንደሌለ መመልከት እንችላለን:: ስለሆነም ቤተክርስቲያን የተጠራቀመ የቤት ሥራ አለባት:: እስላማዊ ጽንፈኛ ቡድን በብርሃን ፍጥነት ምእመናንና ቤተ ክርስቲያንን እያወደመ፤ ቤተ ክርስቲያን ግን እስካሁን ድረስ ሌላ አዲስ የኀዘን ዘመንን ትጠብቃለች:: ምእምናንና ንብረታቸው ከሌለ ሀገርም ቤተ ክርስቲያንም እንደሌለች መረዳት ያስፈልጋል:: ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት ዋና ዋና መሠረታዊ ተግባራትን ልታከናውን ይገባታል:: ተደጋጋሚ ግፍ ከእንግዲህ አልሸከምም በቃኝ ማለት አለባት::

ምእመናንም የተቀናጀ አደረጃጀት ፈጥረው ራሳቸውንና ንብረታቸውን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናቸውን ከእስላማዊ አክራሪ ጽንፈኛ ቡድን ስልታዊ ጥቃት ሊጠብቁ ይገባል:: ይህ ታዲያ ዘመኑን የዋጀ አደጃጀት መሆን አለበት:: ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ድረስ የመረጃ መረብ ፈጥሮ ወንጀልን ቀድሞ መከላከልና ወንጀሉ ሲከሠትም በንቃት የመመከት አቅምን መፍጠር ያስፈልጋል:: አደረጃጀቱ እውነተኛ የሆኑ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎችን ያሳተፈ ቢሆንም ይመከራል::

ዋናውና መጀመሪያ መሠራት ያለበት ምእመናን ተደራጅተው ራሳቸውን እንዲከላከሉ ለሚፈጥሩት አደረጃጀት ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባታል:: ከላይ እስከታች ያለውን አደረጃጀትም ቤተ ክርስቲያን በዋናነት ልትመራው ይገባል:: አደረጃጀቱን በንዋይ፣ በሀሳብና በቁስ መደገፍ ያስፈልጋል:: በየዘርፉ ያሉ ምሁራን የቤተ ክርስቲያንም ልጆች መእመናንን እንዲያግዙና እቅድ እዲያወጡ ማድርግ አስፈላጊ ነው::

የቤተክርስቲያኒቱ ልጆች ምሁራንም ለሚፈጠሩት ችግሮች ሁሉ ቅደመ ትንታኔና ድኅረ ትንታኔ እንዲሰጡ ቢደረግ መልካም ነው:: ከእነዚህ ዋና ዋና ተግባራት በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ለሞቱባት ምእመናን ለጠፋው ሀብትና ንብረት የሚሆን ተመጣጣኝ ካሣ መንግሥት እንዲከፍል ማድረግ ይጠበቅባታል:: በየጊዜው በእስላማዊ አክራሪ ጽንፈኛ ቡድን የተፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን የሚያሳዩ የተደራጁ መረጃዎችን ለሀገሪቱ መንግሥትም ሆነ ለውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች፤ መንግሥታት እንዲሁም ለሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ማስገባት ይገባታል:: ቤተ ክርስቲያናችንንና ምእመናንን ከእስላማዊ አክራሪ ጽንፈኛ ቡድን የተቀናጀ ጥቃት የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ በቸርነቱ ይጠብቅልን:: አሜን!!!

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር!*

# ዓይን የላቸውም ዓይን ያለንን ግን ይመሩናል፣ እጅ የላቸውም ያሰሩናል . . .

ክፍል ሁለት

ከቆየ እትም የተወሰደ

*የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትም ደግሞ ክፍል ሁለትና የመጨረሻውን ክፍል ይዘንላችሁ ቀርበናል። መልካም ንባብ።*

በ፲፱፻፹፰ዓ.ም የተሠራው የዳንዴ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ታሪካዊ ቢሆንም የአካባቢው ምእመናን በተለያዩ ምክንያቶች ወደሌሎች ከተሞች በመሔዳቸው ያሉትም ባለባቸው ችግር በሚገባ ሊንከባከቡት ባለመቻላቸው በመፈራረስ ላይ ይገኛል። የሚያስፈልገው እርዳታ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ የጉዳዩን አሳሳቢነት ለሀገረ ስብከቱ አስታውቀናል። አቅማችን በፈቀደ ግን እየረዳን ነው። ለምሳሌ የነበሩት ካህን ደሞዛቸውን ሊያገኙ ባለመቻላቸው ወደሌላ ከተማ ሔደው ስለበረ ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር ወደቦታው እንዲመለሱ አድርገናል። በተጨማሪም አንድ ሌላ ካህንና ዲያቆን በማምጣት ደሞዛቸውን እየከፈልን በማገልገል ላይ ናቸው።

ሌላው የአቡነ ኤውስጣቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በሸበዲኖ አካባቢ ከአረንጓ መድኃኔዓለም ቀጥሎ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም የተሠራ ነው። ይሁን እንጂ ፲፱፻፷፮ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ወቅት ይረዱት የነበሩት ባላባቶች በመበተናቸው ችግር ላይ ወድቋል።

ይህ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳው ተሰነጣጥቆ ስለበረ ተለስኖ ቀለም ተቀብቷል፤ ወለሉም ዙሪያው ውኃ ልክ ተሠርቶለት ሊሾ ሆኗል። የመቅደሱም ጣራ ስለሚያፈስ ጥላ ተዘርግቶ ነበር የሚቀደሰው ስለዚህም የመቅደሱን ቆርቆሮ አስለውጠናል። አዲስ የታቦት መንበርም አሠርተናል። የተጓደሉ አልባሳትንና ንዋያተ ቅድሳትም እንዲሟሉ አድርገናል። የልዑካኑም አልባሳት የተሟሉ ባይሆንም ለአንድ ካህን እየከፈልን በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

የአቡነ ኤውጣቴዎስን ገድልም ካለበት ከሰሜኑ የአገራችን ክፍል በማፈላለግ በብራና አጽፈን አስመጥተናል።

በሀገረ ሰላም የሚገኘው ታሪካዊውን የሁርሶ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳምም እየረዳን ነው። በ፲፱፻፹፰ዓ.ም ሽፍቶች የአካባቢውን ሕዝብ ሲገድሉና አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥሉ ይህንንም ገዳም ለማፍረስ ሞክረው ነበር። ይሁን እንጂ የነብር መንጋ ስላሳደዳቸው ሳይሳካላቸው ቀርቷል። በተለይ አንድ ነብር ጽላቱ ወደ ሀገረ ሰላም ማርያም ሲሄድ እዚያው ድረስ አጅቦ አንደ አደረሰውና በኋላም ጽላቱ ሲመለስ ቤተ ክርስቲያኑ ሲከፈት በመቅደሱ ውስጥ ተኝቶ መገኘቱን ሲሔድም ሰላምታ ሰጥቷቸው መሔዱን ካህናቱና የአካባቢው ምእመናን መስክረዋል ያ ነብር አሁንም በየቀኑ ይመጣል።

ይህ ቤተ ክርስቲያን እስከ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ተዘግቶ ቆይቷል። ችግሩን የተመለከቱ የአካባቢው ምእመናን በገለጹልን መሠረት ለ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ፍልሰታ ማስቀደሻ የሁለት ካህናት፣ የሦስት ዲያቆናት አስፈላጊ ወጪዎችና ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮች በማሟላት አሥራ ስድስቱንም ቀናት ሰዓታት ተቆሞና ተቀድሶ በዓሉ ተከብሯል። ከዚያም አንዱን ካህንና ሁለቱን ዲያቆናት ቀጥረን እያገለገሉ ነው።

ከ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ ወጥቶና ነግሦ የማያውቀውንም ታቦተ ሕግ መጋቢት ፳ ቀን፲፱፻፺ዓ.ም የንግሥ በዓሉን አክብረናል። ወደሌላ የእምነት ድርጅቶች ሔደው የነበሩ ምእመናንም በየጊዜው በሚላኩት መምህራን በተሰጠው ትምህርት እየተመለሱ ነው። የሰንበት ትምህርት ቤትም ተቋቁሞ አበረታች እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

ቀደም ሲል ተፈጥሮ በነበረው ግርግር በየመንደሩ ተቀምጠው የነበሩ ብዙ ንዋያተ ቅድሳትና አልባሳት ጠፍተዋል:: ያሉትም በመጎዳታቸው አገለግሎት መስጠት አይችሉም:: ይህን ችግር ለማቃለል ለጊዜው የአምስት ልዑካን ልብስ ገዝተን አስገብተናል:: ችግሩ ግን በቀላል የሚወገድ አይደለም:: ለምሳሌ ጻሕል፣መቁረርት፣ መጎናጸፊያም፣ መጻሕፍትና የመሳሰሉት አልተሟሉም:: ሕንፃውም የሲሚንቶና የባለሙያ ችግር ስለገጠመው እንጂ ለመጠገን በዝግጅት ላይ ነን:: በጅምር የቀሩ በሮችንና መስኮቶችንም ለማጠናቀቅ ዕቅድ ይዘናል::

ከአዋሳ ብዙም የማይርቀው ሌላው ቤተ ክርስቲያን የጻድቁ የገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ነው:: በሸበዲኖ ወረዳ በሞርቾ አካባቢ የሚገኘው ይህ ቤተ ክርስቲያን የተሠራው በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ሲሆን በመቃኞ መልክ የተሠራ ነው:: በመንገድ ዳር የሚገኝ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ‹‹ችግር አይኖርበትም›› እያልን እያለፍነው እንሄድ ነበር:: ውስጡን ስናየው ግን በጣም የተጎዳ ቤተ ክርስቲያን ነው:: የአካባቢው ምእመናንም ቁጥር ጥቂት ነው::

ስለዚህም በግንቦት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም የበፊቱን መቃኞ በማፍረስ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተጀምሮ አሁን ሥራው ወደመጠናቀቁ ነው:: በዚህ ሥራ በአዋሳና በይርጋዓለም የሚገኙ ምእመናን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው:: የአቡነ አረጋዊ ጽላት በድርብነት እንዲገባ የቀረበው ሃሳብም የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ የብፁዕ አቡነ በርቶሎሜዎስን መልካም ፈቃድና ጥረት በማግኘቱ የሕንፃውን መጠናቀቅ በመጠባበቅ ላይ ነን::

በይርጋዓለም የማስተባብራቸው ምእመናንም ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ ነው:: በ፲፱፻፺፱ዓ.ም የካቲት ወር ለጸበል ይርጋዓለም ሔጄ በነበረበት ወቅት የአዋሳውን እንቅስቃሴ የነገርኳቸው አባቶችና ወጣቶች አብረውን ለመሥራት በመፍቀዳቸው በጀመሪያ በአቅራቢያው የምትገኘውን የሺሻ ማርያምን ለማደስ ወሰንን:: ሺሻ ማርያም በይርጋዓለም አካባቢ በዳሌ ወረዳ የምትገኝ በተራራ ላይ የሠራች ቤተ ክርስቲያን ነች::

ለትራንስፖርት አስቸጋሪ በመሆኗ ይህች ቤተ ክርስቲያን ለማደስ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስ በሸክም በማውጣት እናቶች ሳይቀሩ አስተዋጸኦ አድርገዋል:: ብዙ እናቶች አሸዋ በአንስራ እየሞሉ አውጥተዋል:: በዚህም ወለሉ ሊሾ ተደርጓል፣ ተጎድቶ የበረው ግድግዳ ተጠግኗል:: በርና መስኮቶችንም ከከተማ በማስመጣት አስገጥመናል:: የምእምናኑ ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑም አዲስ መንበርና ሙሉ አልባሳት ለማሟላት ተችሏል:: ሰንበት ትምህርት ቤቱም እየተጠናከረ ነው::

በሸበዲኖ ወረዳ ወንዶ ጢቃ አካባቢ የሚገኘውን የጋንጌሶ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም በመርዳት ላይ ነን:: በ፲፱፻፵፰ዓ.ም በመቃኞ መልክ ተሠርቶ ከእርጅና የተነሣ አጋድሎ የሚታይ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ለመግባት እንኳን ያስቸግር የነበረውን ይህን መቃኞ በማፍረስ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል:: ሥራው ግን ሙሉ በሙሉ አልተጠናቀቀም:: ኮርኒስ፣ አጥርና ሌሎችም ሥራዎች ይቀራሉ:: በሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋምና እንዲጠናከር፣ በየሳምንቱ እሑድና በዕለተ ቅዱስ ሚካኤል እንዲቀደስ፣ የነበሩትም ካህን አንድ ብቻ ስለበሩ አንድ ካህንና አንድ ዲያቆን በተጨማሪ ወጪያቸውን በመሸፈን ለማሠራት ተችሏል:: በአጠቃላይ የይርጋዓለም እንቅስቃሴ አነሣስና አካሔድ ይህን ይመስላል::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የምትረዷቸው አብያተ ክርስቲያናት ባሉበት አካባቢ የሚገኙትን ምእመናን ስለ አገልግሎታችሁ ምን አስተያየት አላቸው?

***አባ ዜና ገብርኤል፡-*** የአካባቢው ምእመናን በጣም ነው የሚደሰቱት:: በገንዘብም በጉልበትም ይረዱናል:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ሲያገኙን ያለቅሳሉ:: ችግራቸውን የሚያይ ሰው ይፈልጋሉና ደስተኞች ናቸው::

ለምሳሌ በሲቄ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የምእመናን ብዛት አናሳ ነበር:: በሰንበት እንኳ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣ ሰው አይገኝም ነበር:: የነበሩት ካህንም ብቻቸውን መታግል ተስኗቸው ነበር:: በኋላ ከእኛ አገልግሎት መጠናከር ጋር ግን ሁሉም ተነሣሱ:: በሚሰጠውም ትምህርት የምእመናን ቁጥር እየበዛ ነው:: ሰበካ ጉባኤውም እየተጠናከረ ነው:: በሌሎችም ቦታዎች ያለው ሁኔታ የሚያበረታታ ነው::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ለምእመናን የሚያስተላልፉት መልእክት አለ?

***አባ ዜና ገብርኤል፡-*** አዎ ማለት የምፈልገው ነገር አለ፡፡ ምእመናን የሚደነቁትንና በብዛት የሚታወቁትን ብቻ ሳይሆን በየገጠሩ የሚገኙትን ብዙ ቅርሶችን የያዙትንና በመፈራረስ ላይ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ሊያስታውሱ ይገባል፡፡ በተለይ ወጣቶች በየገጠሩ ለመናፍቅነትና ለሱስ የተዳረጉትን ወንድሞቻችን ፈለግ ተከትሎ በየገጠሩ ማስተማርም ይገባል፡፡ ዛሬ ብርቅና ድንቅ የምንላቸውን አብያተ ክርስቲያናት አባቶቻችን ባይጠብቁልን ኖሮ አናያቸውም ነበር፡፡ ስለዚህ እኛም ለተተኪው ትውልድ የምናወርሰው እንዳናጣ መትጋት ይኖርብናል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በመጨረሻ ወደ ግል ሕይወትዎ ለመለስና አካል ጉዳተኝነትዎ በአገልግሎትዎ ላይ የፈጠረብዎት ችግር አለ?

***አባ ዜና ገብርኤል፡-*** እውነት ለመናገር አካል ጉዳተኝነቴ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ብዙም ችግር አልፈጠረብኝም፡፡ ምክንያቱም ወንድሞቼና እኅቶቼ ልጆቼ ሳይጸየፉና ሳይኮሩ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ያደርጉልኛልና ነው፡፡ መሔድ በምፈልግበት ጊዜ እየተሸከሙ ወደመኪናዬ በማውጣትና በማውረድ በመሳሰሉት ይደግፉኛል፡፡

ይልቅ ከሚሠሩት አድካሚ ሥራ በተጨማሪ እኔን እየተሸከሙ ሲወጡና ሲወርዱ ቅሬታ ይሰማኛል፡፡ ሙሉ አካል ኖሮኝ እኔም እንደእነሱ ብሠራ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ድሮ ድሮ ስለ በሽታዬ አስብ ነበር፡፡ አሁን ግን የማስበው ‹‹ይህች ቤተ ክርስቲያን ተጀምራለች መቼ ትፈጸም›› ይሆን? ወንድሞቼንና እኅቶችን አስቀይሜያቸው ይሆን? እያልኩ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር እኔን ደካማውን ምክንያት አድርጎ ወገኖቼ ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ሲተጉ ስመለከት ደስታ ይሰማኛል፡፡ ደግሞም እኮ እንዲህ ባልሆን ኖሮ አሁን የምሠራውን አልሠራ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ግን ሁሉን ለበጎ አድርጎታል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** አባታችን እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜን ያድልልን፡፡ በአገልግሎትዎ ያጽናልን፡፡ ቃለ ምልልሳችንን የምናቆመው የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መምህር ኃይለ ሥላሴ ስለ አባ ዜና ገብርኤል የተናገሩትን ጠቅሰን ነው፡፡

‹‹እጅ የላቸውም እጅ ያለንን እየሠሩ ያሠሩናል ዐይን የላቸውም ዐይን ያለንን ይመሩናል እግር የላቸውም እግር ላለን እንዴት እንደምንራመድ ያስተምሩናል››

ከአባ ዜና ገብርኤል ሕይወት ብዙ ነገር እንማራለን፡፡ እጅ፣ እግር፣ ዓይን ባይኖራቸውም እግዚአብሔርን አላማረሩም፡፡ ቅዱስ ዳዊት ‹‹እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ›› /መዝ፡)”፬.፮/ ያለው በጸጋ ተቀበሉት እግዚአብሔርም በአኰቴት ፈቃዱን መቀበላቸውን ዓይቶ የበለጠ ሥራ አሠራቸው፡፡

ዛሬ ሙሉ አካል፣ ጊዜው፤ ዕውቀቱና ሀብቱ ኖሯቸው በእምነት ጸንተው በመከራ ታግሠው፣ እምነታቸውን በመልካም ሥራ የሚገልጡ ሰዎችን ማግኘት እጅግ ከባድ ነው፡፡ ስለጉድለቱ፣ ስለመከራው ይቅርና በየዕለቱ በሕይወቱ ውስጥ ስለተደረጉ የእግዚአብሔር የቸርነት ሥራዎች የሚያመሰግኑ ከናፍር ነጥፈዋል፡፡

ሀብት፣ ንብረት ያላቸው የሰጣቸውን ተመልክተው በተሰጣቸው ለቤተ ክርስቲያን፣ ለወገንና ለሀገር የሚበጅ በምድርም በሰማይም ክብርና ዋጋ ያለውና የሚያሰጥ ሥራ ከመሥራት የአካላቸውን ውበት የሀብታቸውን ብዛት፣ የዕውቀታቸውን ምጥቀት በማየት የሥጋ አንቱዎች የነፍስ ጉስቋሎች ብዙዎች አሉ፡፡

ስለዚህ እንደ አባ ገብርኤል የበኩላችንን እግዚአብሔር እንደፈቀደልን ለመሥራት ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ ልብ ይኑረን እግዚአብሔር ደግሞ የበለጠ ያሠራናል፡፡ የልብ መዘጋጀት ከሰው ነው የምላስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር ነው እንዳለ ከሁሉ አስቀድሞ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተዘጋጀ ልብ ይኑረን፡፡ በመጨረሻ ይህን ቃለመጠይቅ አድርገው ከተሟሉ መረጃዎች ጋር ለዝግጅት ክፍላችን ያደረሱንን የአዋሳ የንዑስ ማዕከል አባላትን ከልብ እናመሰግናለን፤ ይልመድባችሁ ሌሎች ይከተሏችሁ፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# “የተደራጀ አክራሪ ኃይል ቤተ ክርስቲያንን እያጠቃት እንደሆነ በተደጋጋሚ ለመንግሥት አሳውቀናል”

*ቀሲስ ሙሉቀን ብርሃኑ*

*በኢት/ ኦ/ተ/ቤ/ክ/ ጴጥሮሳውያን የቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት አስጠባቂ ኅብረት ሰብሳቢ*

በካሣሁን ለምለሙ

**ክፍል ሁለት**

*የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትም ደግሞ ክፍል ሁለትና የመጨረሻውን ክፍል ይዘንላችሁ ቀርበናል። መልካም ንባብ።*



*ቀሲስ ሙሉቀን ብርሃኑ*

ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በባህልም ሆነ በሃይማኖት እንዲሁም በሕግ ራሳቸውን የመከላከል መብት አላቸው። የትኛውም ምእመን ራሱንም ሆነ በእምነት የሚመስሉትን የመጠበቅ ኃላፊትነት አለበት። ሌላውን ማጥቃት ሳይሆን ሌላው ሊያጠቃ ሲል ቀድሞ መከላከል ችላ የማይባል ተግባር መሆን አለበት። በዚህ ሰዓት ኦርቶዶክሳውያን ራሳቸውን ለመላከል ሳይችሉ ቀርተው ወይም አቅሙ ስለሌላቸው ሳይሆን የቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ ስለማይፈቅድ ነው። ክፉን በበጎ እንጂ ክፉን በክፉ መልስ የሚል አስተምህሮ ቤተክርስቲያን የላትምና።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በኦሮሚያ ክልል ባሉ ዞኖችና ወረዳዎች በተደጋጋሚ በኦርቶዶክሳውያንና በንብረታቸው ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ ጥቃት መድርሱ ምንን ያሳያል ይላሉ?

***ቀሲስ ሙሉቀን፡-*** ከዚህ ቀደም እስላማዊው አክራሪ ቡድን የፈጸማቸው ተከታታይ ጥቃቶች በዋናነት አብያተ ክርስቲያናትንና ምእመናንን ዒላማ ያደረገ ነበር። በዚህኛው ጥቃት ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ቃጠሎ ላይ መንግሥት ትኩረት አድርጎ መከላከያ ሠራዊትን በማሰማራት አብያተ ክርስቲያናትን መጠበቅ ሲጀምር እስላማዊው አክራሪ ቡድን ደግሞ ታክቲክ ቀይሮ ምእመናንን፣ ቤታቸውንና ሀብት ንብረታቸውን ማጥቃት ጀመረ። የድርጊቱ ዋና ዓላማ ምእመናን መኖሪያ ቤት ሲያጡና የዕለት ጉርስ ሲርቃቸው አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ ወይም ተቸግረው እንዲሰልሙ ማድረግ ነው። ምእመናን ከሌሉ ደግሞ በየአካባቢው ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ከሕንፃነት የዘለለ ሚና አይኖራቸውም። ከሰሞኑ በአንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች በተከሰሠተው ሃይማኖት ተኮር ጭፍጨፋም ምእመናን እንደተለመደው ቤተ ክርስቲያናቸውን በመጠበቅ ላይ እያሉ እስላማዊው ጽንፈኛ ቡድን የምእመናኑን ቤትና ንብረት ይዘርፍና ያቃጥል ነበር።

በዚህ ሁኔታ ታድያ ኦርቶዶክሳውያኑ በአንድ ጀምበር ከመጽዋችነት ወደ ተመጽዋችነት ተሸጋግረዋል።

ችግሩ እንደ አጠቃላይ የሚያመላክተው አክራሪ ኃይሉ ከኦርቶዶክሳውያን የፀዳች ኦሮሚያን የመመሥረት ሕልም እንዳለው ነው፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ በተደጋጋሚ ከሞራላዊ ልዕልና ያፈነገጠና ጭካኔ የተሞላበት ወንጀልን በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ እየፈጸመ ይገኛል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በኦሮሚያ ክልልና በሌሎች አካባቢዎች እስላማዊው አክራሪ ቡድን በምእመናን ላይ በሚፈፅማቸው የወንጀል ድርጊቶች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የጸጥታ ኃይሎች ቀጥተኛ ተሳታፊ እንደሆኑ ይነገራልና ይህን እንዴት ይገልፁታል? በዚህ ሁኔታስ ሀገሪቱ ወዴት እያመራች ነው ይላሉ?

***ቀሲስ ሙሉቀን፦*** እውነት ነው አንዳንድ የመንግሥት አካላትና የፀጥታ ኃይሎች ከእስላማዊው አክራሪ ቡድን ጋር አብረው በጋራ እየሠሩ መሆናቸው ለእኛ አዲስ አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ ሁልጊዜ ለከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች አዲስ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ግን መንግሥት ማመን የማይፈልገውን ጉዳይ ተገዶም ቢሆን ማመን ችሏል፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ዓመት በሶማሌ ክልል በጅግጅጋና አካባቢው የተፈፀመው ጥቃት በክልሉ ርእሰ መስተዳድርና በክልሉ ካቢኔ ተወስኖ የተፈጸመ ነበር፡፡ በዚያ ወቅትም የክልሉ ልዩ ኃይልና "ሄጎ" በሚል ስያሜ የተደራጀው የጥፋት ኃይል ነበር በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ አሰቃቂ ጥቃት የፈጸመው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሲዳማ ክልል የተፈጸመውንም ጥቃት ይመሩ የነበሩት የአካባቢው ባለሥልጣናት ነበሩ፡፡ በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ እየተፈጸመ ያለው ጭፍጨፋም በባለሥልጣናቱና በፀጥታ ኃይሉ የሚመራ ነው፡፡

በአንድ ወቅት የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን በጥቃት የሞቱ ኦረቶዶክሳውያን አስክሬን እንዳይቀበር እስከመከልከል ደረጃ እንደደረሰ እናስታውሳለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ግለሰብ በኦሮሚያ ክልል ኦርቶዶክሳውያን የጠሩትን "የመብታችን ይከበር" ሰላማዊ ሰልፍ ከልክሎ ሙስሊሙ ግን ሰልፍ እንዲወጣ የፈቀደ ግለሰብ ነው፡፡ ስለዚህ በኦሮሚያ ክልል ኦርቶዶክሳውያንን ሰልፍ መከልከል ምንም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በአንድ ሀገር እየተኖረ ግለሰቡ ለሙስሊሙ የተለየ መብት ሰጭ ሆኗል፡፡ በክልሉ በተለያዩ ጊዜያት በምእመናን ላይ የደረሱ ጥቃቶችን ይመሩና ያስተባብሩ የነበሩት ፖሊስ ኮሚሽነሮችና የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊዎች ናቸው፡፡ የተደራጀው እስላማዊ አክራሪ ቡድን ከየወረዳውና ቀበሌው ተሰባስቦ ምእመናንን ለማጥቃት ወደከተማ በሚገባበት ወቅት ከላላና የሎጅስቲክ አቅርቦት ሲያደርግ የነበረው "የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ ነኝ" የሚለው አካል ነው፡፡ በዚያን ወቅት በእነዚህ አካላት ላይ መንግሥት ቀደም ብሎ አስተማሪ ርምጃ ወስዶ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ትርምስ ባልተፈጠረ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች በአንድ በኩል የመንግሥት ሥልጣን ይዘው በሌላ በኩል ደግሞ ከጽንፈኛ እስላማዊ ቡድን ጋር ወግነው ምእመናንን በየጊዜው በጭካኔ ያሳርዳሉ፡፡ የአርቲስት ሀጫሉን ሞት ሽፋን አድርገው አክራሪዎቹ በምእመናን ላይ ጥቃት ሲፈጽሙ የምዕራብ አሩሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሄኖክ ለፖሊስ ኮሚሽነሩም ሆነ ለፀጥ ዘርፉ ኃላፊው ስልክ ደውለው "ድረሱልን" የሚል ተማፅኖ ሲያቀርቡ "እሺ" የሚል ምላሽ ከሰጡ በኋላ ስልካቸውን ዘግተው የውኃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል፡፡ እነዚህ የፀጥታ አካላት ድሮም ይሠሩት የነበረውን አሁንም ያለ ከልካይ እየሠሩ ነው፡፡ ሀገር እንደ ሀገር እንድትቀጥል ከተፈለገ በመንግሥት ወንበር ላይ ተቀምጠው የሃይማኖትን ጉዳይ በሚያስፈፅሙ የፀጥታ አካላት ላይ አስተማሪ ርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ እነዚህ አካላት ከአክራሪ እስላማዊ ቡድን የተሰጣቸውን ተልእኮ እየፈጸሙና እያስፈጸሙ ሊቀጥሉ አይገባም፡፡

በሀገሪቱ ሰላም እንዲወርድ ከተፈለገ "የፀጥታ ኃይል ነን" ብለው የሃይማኖት ተልእኮን የሚያስፈፅሙት ላይ አስተማሪ ርምጃ ከተወሰደ ሌላው ነገር እጅግ በጣም ቀላል ነው፡፡ ሎጀስቲክና ከለላ የሚሰጣቸውን አካል ከሕግ ፊት ማቆም ከተቻለ ሌላው ባልበሰለ ጭንቅላቱ ሊገድልና ሊዘርፍ የሚመጣውን ለመቆጣጠር ዘዴው ቀላል ይሆናል፡፡ በአብዛኛው የሕይወትና የንብረት ጉዳቶች የተፈፀሙት ከንቲባዎችና የፖሊስ አባላት በታዛቢነት ቆመው ይመለከቱ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ ይህ እጅግ ያሳዝናል፡፡ ሀገሪቱስ ወዴት እየሄደች ነው? ያስብላል፡፡

ስምዐ ጽድቅ፡- ጥቃት ከተፈጸመ በኋላ ምእመናን በከፍተኛ ሥጋት ውስጥ ባሉበት ወቅት አንዳንድ የአካባቢው የፀጥታ ኃይል ምንም እንዳልተፈጠረ ጉዳዩን ሲያቃልሉት በተደጋጋሚ ይስተዋላልና ይኽ ምን ማለት ነው?

***ቀሲስ ሙሉቀን፡-*** የመጀመሪያው ሌላውን አካል ለማረጋጋት የታቀደ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአብዛኛው በሚዲያ ቀርበው ማብራሪያ የሚሰጡት አጥቂዎቹ የፀጥታ ኃይሎች ናቸው። እነዚህ አካላት ጥቃቱን የመሩ፣ ድጋፍ የሰጡ፣ ያበረታቱ፣ ሎጀስቲክስ ያቀረቡና ለአክራሪዎች ከለላ የሰጡ ናቸው። በዚህ ሁኔታ ታዲያ የፈጸሙት በደል እንዳይታወቅባቸው የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ሁሉ ምንም እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ያወራሉ፤ በሰው ደምም ይቀልዳሉ። መረጃም ሲጠየቁ የሚፈልጉትን እንጂ እውነቱን እየተከናወነ ያለውን ነገር ለሕዝብ ይፋ አያደርጉም። መከላከያና የክልሉ ልዩ ኃይል ፀጥታን ለማስከበር ወደ አካባቢው ሲሄዱ "ተቆጣጥረነዋል ምንም ችግር የለም" እያሉ የሚመልሱ አካላት ናቸው።

ስለሆነም ችግሩ መች እንደሚቆም ስላማይታወቅ ወጣቱ ተደራጅቶ ራሱንና ቤተክርስቲያኑን እንዲጠብቅ እንመክራለን። ችግሩ ከዚህ በኋላ ደግሞ የት እንደሚፈጠር አናውቅም። ሙስሊሙም፣ ፕሮቴስታንቱም፣ ፖለቲከኛውም፣ ብሔርተኛም እንዲሁም ዘረኛው ሲያኮርፉ የእልሁ መወጫ የሚያደርጓት ቤተ ክርስቲያንን ስለሆነ ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል። ሀገርን የማፍረስ ተልእኮ ያነገበ ሁሉ መጀመሪያ የሚያጠቃው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ነው። ቤተ ክርስቲያንን ቀድሞ ካላጠቃ ሀገርን ማፍረስ አይችልም። ሀገርን ለማፍረስ ደግሞ የኢትዮጵያን ሚዛን ጠብቃ የያዘችውንና ለነርሱ ሀገርን የማፈረስ ተልእኮ ደንቃራ የሆነችባቸውን ቤተ ክርስቲያንን አስቀድመው ለማፍረስ ያልማሉ።

አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎችና ሌሎች የመንግሥት አካላት ለአክራሪ ሙስሊም ከለላ እየሰጡ በምእመናን ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ከማደርግ በዘለለ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የተሳሳተ መረጃ ሲሰጡ ነበር። መከላከያ ሠራዊት ችግሩን ለማረጋጋት በሚሄድበት ወቅት "እኔ ሳልፈቅድ ለምን ገባህ" የሚሉ የዞን አመራሮች ባሉበት አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች እንዴት ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ይቻላል? የእነዚህ አካላት ዓላማ ጉዳዩ ተድበስብሶ እንዲቀር፤ ተጨማሪ ንብረትና ሕይወት እንዲጠፋና ተልእኮ የሰጣቸውን አካል በማስደሰት ዓላማው እንዲሳካ ማድረግ ነው። ከዚያም ባለፈ ጥቃቱ እንዲቀጥልና ሕዝብ ክርስቲያኑ በፀጥታ ችግር ምክንያት ተማሮ ሀገሩን ጥሎ እንዲሄድ ማድርግ የመጨረሻ ግባቸው ነው። ምእመናኑ ቤታቸው ተቃጥሎ፤ ንብረታቸው ተዘርፎ የሚላስ የሚቀመስ ሲያጡ ሀገሩን ለቀው ሲወጡ ማየት ሕልማቸው ነውና እንዲወጡ ከየአካባቢው ተሰባስቦ የሚሄድላቸውን ሰብአዊ ርዳታ እንዳይጠቀሙም መንደርተኛ የዞን አመራሮች እርዳታውን ይመልሳሉ። ይህንን ጭካኔ የተሞላበት ውስብስብ የወንጀል ድርጊት ከማሳወቅ አንጻር ሚዲያዎች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው።

**አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎችና ሌሎች የመንግሥት አካላት ለአክራሪ ሙስሊም ከለላ እየሰጡ በምእመናን ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ከማደርግ በዘለለ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የተሳሳተ መረጃ ሲሰጡ ነበር። መከላከያ ሠራዊት ችግሩን ለማረጋጋት በሚሄድበት ወቅት "እኔ ሳልፈቅድ ለምን ገባህ" የሚሉ የዞን አመራሮች ባሉበት አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች እንዴት ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ይቻላል? የእነዚህ አካላት ዓላማ ጉዳዩ ተድበስብሶ እንዲቀር፤ ተጨማሪ ንብረትና ሕይወት እንዲጠፋና ተልእኮ የሰጣቸውን አካል በማስደሰት ዓላማው እንዲሳካ ማድረግ ነው።**

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በቤተ ክርስቲያን ስም የተቋቋሙት የማኅበራት ኅብረት በዘላቂነት የቤተ ክርስቲያንና የምእምናን ክብርና መብት ለማስጠበቅ ምን እየሠሩ ይገኛሉ?

ቀሲስ ሙሉቀን፡- ሁልጊዜም እንደዚህ ዓይነት መሰል ችግሮች ሲከሠቱ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ሁሉ ጥቃቱ ከሚፈጸምበት ቦታ ያገኘነውን መረጃ እናሳውቃቸዋለን፡፡ እየተፈጸመ ያለውን የወንጀል ድርጊት ሁሉ ሳይቆራረጥ ለመንግሥት አካላት በየጊዜው እናሳውቃለን፡፡ በዚህ መነሻነት ከመንግሥት አካላት ጋር በምንችለው መጠን እስካሁን እየሠራን እንገኛለን፡፡ አሉ የሚባሉ መረጃዎችን ሁሉ አደራጅተን ለቋሚ ሲኖዶስ አስገብተን ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩን በትኩረት እንድታየው ጥረት እያደርግን ነው፡፡ ጥቃቱን ለመከላከል መፍትሔው ብዙ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ለተፈጠረው ችግር ሁሉ መፍትሔ እንድትሰጥ፣ልጆቿን እንድትጠብቅና ልጆቿም ራሳቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ ያለባትን ሁሉ እንድታደርግ መረጃዎችን ከመጀመሪያ አንሥቶ እስከ መጨረሻው አስገብተናል፡፡ በተጨማሪም በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ ጭፍጨፋ ባወጁ ሚዲያዎች ለአብነትም OMN (ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ) የተባለውን የግል የቴሌቭዥን ጣቢያ በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ከሰን በሕግ እንዲጠየቅ ጥረት ያደረግን ቢሆንም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ግን ምንም ዓይነት ሕጋዊ ርምጃ ሲወስድበት አላየንም ከዚህ ቀደም ርምጃ ባለመወሰዱ ይህ ሚዲያ በአርቲስት አጫሉ ሁንዴሳ ሞት ማግስት ባሰራጨው ተጨማሪ የዘር ጭፍጨፋ መረጃ ብዙ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በግፍ ተገድለዋል፡፡ ሀብት ንብረታቸው ተዘረፈ፤ የተረፈው ተቃጠለ፡፡ በሕይወት የተረፉ ምእመናንም በረሀብ አለንጋ እየተገረፉ ናቸው፡፡ ሌሎቹም ቀያቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣናቱ በወቅቱ መደረግ የነበረበትን ቢያደርጉ ኖሮ ይህ ሁሉ ቀውስ ባልተከሠተ ነበር፡፡ አሁን እኛችን ላይ በርካታ መረጃዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን መረጃዎች ተጠቅመን ክስ ለመመስረት ለዐቃቤ ሕግ አደራጅተን እየሰጠን ነው፡፡

አንዳንዴ ኢስላም "ሰላም ነው" ይላሉ፤ ግን ሰላምነቱ በተግባር የት አለ? "ሃይማኖቴ ሰላም" ነው ካለ ከጅግጅጋ እስከ ኦሮሚያ ኢስላም በሚበዛባቸው አካባቢዎች ክርስቲያኖችን የሚገድልና የሚያስገድልን አክራሪ እስላማዊ ቡድን ማስቆም አለበት፡፡ የሰላም ነው የሚለው አካል ይህን አረመኔያዊ ድርጊት ሊያወግዝ ይገባል፡፡ ይህንንም በተግባር ሊያሳይ ይገባል፡፡ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤውስ ምንድን ነው እየሠራ ያለው? ድርጊቱን የሚያወግዘው መቼ ነው? መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ ያለባቸው ለቤተ ክርስቲያን ብለው ሳይሆን ለሀገር አንድነትና በፖለቲካ ሥልጣናቸው መቆየት እንዲችሉ ነው፡፡ መንግሥት በመንበሩ መቆየት ከፈለገና ፓርቲዎች ሥልጣን መያዝ ከፈለጉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ አለባቸው፡፡ ካልሆነ ግን የኢትዮጵያ የአንድነት ምሰሶ ተናግቶ የሀገር አንድነት አይታሰበም፡፡ ፖለቲካና ሥልጣን የሚኖረው ሀገርና ሕዝብ ሲኖር ብቻ ነውና፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?

***ቀሲስ ሙሉቀን፡-*** በዚህ ወቅት ከምንጊዜውም በላይ ቤተ ክርስቲያናችንን፣ እራሳችንንና ሀገራችንን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ሀገር ያለ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም ያለ ሀገር አይኖሩም፡፡ ሁለቱ የማይነጣጠሉና አንዱ የሌላው ህልውና መሠረት ሆነው የሚኖሩ ናቸው፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እየተፈጸመ ያለው ነውረኛ ድርጊት የቤተክርስቲያንን ውለታ የካደ በመሆኑ ፖለቲከኞችም፣ ሃይማኖተኞችም፣ ብሔርተኞችም እንዲሁም ጽንፈኞች ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባል፡፡ ተከባብረን ተፈቃቅረንና በሃይማኖት እኩልነት አምነን ልንኖር ይገባል፡፡ ካልሆነ ግን ለሁላችን የማትሆን ሀገር ለማንኛችንም አትሆንም፡፡ ወደ መጠፋፋት ከመሄዳችን በፊት ቆመን ማሰብ ብንችል መልካም ነው፡፡ በተለይ በክርስቲያኖች ላይ ጥቃቱ እየተፈጸመ ያለው እስልምና በሚበዛባቸው አካባቢዎች ነውና እዚያ አካባቢ ያሉ የሙስሊም ሽኮች፣ ኡስታዞች፣ ኡለማዎችና ሌሎች የሀገር ሽማግሌዎች ልጆቻቸውን ማስተማርና መምከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ልጆቻቸው የማንም ፖለቲከኛና አክራሪ ኃይል መጠቀሚያ መሆን የለባቸውም፡፡ "አክራሪ እስላሞች እኛን አይወክሉም" በማለት ወንጀለኛውን በትክክል አሳልፈው መስጠት አለባቸው፡፡

# የዋሁ ነቢይ

ቀሲስ ዘክርስቶስ ጸጋዬ

ተወዳጅ የሆናችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ከርማችኋል? በእግዚአብሔር ጥበቃ በሰላምና በጤና እንደቆያችሁን ተስፋ እናደርጋለን፤ በቤታችሁ ሆናችሁ ትምህርታችሁን በንቃት እየተከታተላችሁ ነው? በጣም ጎበዞች! በመንፈሳዊም በሥጋዊም ዕውቀት ማደግ ይኖርባችኋልና በርቱ!

ልጆች! ዛሬ ስለአንድ ነቢይ ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናል፤ በጥሞና አንብቡ እሺ! መልካም።

ዮናስ የሚባል አንድ ነቢይ ነበር፤ የስሙ ትርጉሙም ርግብ ወይንም የዋህ ነው። በአንድ ወቅትም እግዚአብሔር አምላክ ‹‹ተነሥተህ ወደ ታላቂቱ ነነዌ ሂድ ከክፋታቸው እንዲመለሱ ስበክ›› በማለት አዘዘው። ዮናስ ከትውልድ ሀገሩ ወጥቶ በአሕዛብ ሀገር እግዚአብሔርን ወደማያውቁ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከ ብቸኛ ነቢይ ነው።

እግዚአብሔር ሲያዘው ዮናስ ግን እግዚአብሔር መሐሪ ስለሆነ ‹‹ከጥፋት ቢያድናቸው ውሸታም እባላለሁ›› ብሎ ፈርቶ በጀልባ ከነነዌ ወጣና ከእግዚአብሔር ፊት እምቢ ብሎ እግዚአብሔር ፊት ለመሸሽ ተነሣ። ኢዮጴም ወደምትባል ሀገርም ሄደ። ወደ ተርሴስ የምታልፍ መርከብ አገኘ። ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ወደ ተርሴስ ይሄድ ዘንድ ዋጋ ከፍሎ ወደ መርከቧ ገባ።

እግዚአብሔርም ዮናስ በተሳፈረበት መርከብ በምትጓዝበት ባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስ አመጣ። ማዕበልም ተነሣ፤ መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች፤ መርከበኞቹም ፈሩ፤ እያንዳንዳቸውም ወደ አምላካቸው ጸለዩ። መርከቢቱ ከማዕበሉ አደጋ ድና ጉዞዋን እንድትቀጥል በውስጧ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉት፤ መርከበኞቹ ያንን ሁላ ጭንቀት ሲጨነቁ ዮናስ ግን እንቅልፉን ተኝቶ ነበር።

የመርከቡ አለቃ ወደ አንቀላፋው የዋሁ ነቢይ ወደ ተኛበት ቀርቦ ‹‹ምነው ተኝተሃል? ተነሥተህ አምላክህን ጥራ›› አለው፤ ዮናስም ከእንቅልፉ ተነሣ። መርከቡም በማዕበል እንደተናወጸችና ተሳፋሪዎቹም እንደተጨነቁ አየ። መርከበኞቹ እርስ በርሳቸው ‹‹ይህ ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንዳገኘን እናውቅ ዘንድ ኑ ዕጣ እንጣጣል›› ተባባሉ፤ ዕጣም ተጣጣሉ።

ልጆች ዕጣው በማን ላይ የሚወድቅ ይመስላችኋል?

ዕጣው ከእግዚአብሔር ሊሰወር ሊሸሽ በሞከረው በዮናስ ላይ ወደቀ። ዮናስንም ‹‹ማዕበሉ እንዲቆም ምን እናድርግ?›› አሉት። ዮናስም ‹‹ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንዳገኛችሁ አውቃችኋለሁና እኔን ወደ ባሕሩ ጣሉኝ፤ ያን ጊዜ ባሕሩ ጸጥ ይልላችኋል›› በማለት ነገራቸው።

ምንም እንኳን ዮናስ በራሱ ላይ ቢፈርድም ሰዎቹ ግን እርሱን ለማዳን ወደ ምድር ለመቅዘፍ ሞከሩ። ነገር ግን ባሕሩ አብዝቶ ይናወጥ ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር እንዳያዝንባቸው ጸልየው ዮናስን ወደ ባሕሩ ጣሉት። ባሕሩም ከመናወጥ ጸጥ አለ። ሰዎቹ እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ ስዕለትም ተሳሉ።

እግዚአብሔር ዮናስን የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አንበሪ አዘጋጀ። ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ቆየ። በዓሣ አንበሪው ሆድ ውስጥ ሆኖ እጅግ ስለተጨነቀ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ ልመናም አቀረበ። እግዚአብሔርም የዮናስን ጸሎት ሰማ። ዓሣውንም አዘዘው፤ ዓሣውም ዮናስን ወስዶ በየብስ (በምድር) ላይ ተፋው።



ልጆች! እግዚአብሔር የሚያዘንን እየፈጸምን በታማኝነት ማደግ አለብን:: የትም ብንሄድ ወይንም በየትኛውም ቦታ ብንደበቅ እግዚአብሔር ያየናል:: ከፊቱም መሸሽ አይቻልም:: እግዚአብሔርን በመከራ ጊዜም ስንጠራው ጸሎታችንን ሰምቶ ያድነናል:: በመከራም ጊዜም እግዚአብሔርን መለመን ይገባናል::

ዮናስ ከዓሣ አንባሪው ሆድ ከወጣ በኋላ ወደ ታላቂቱ ከተማ ነነዌ ሄደ:: ‹‹ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፤ ንስሐ ግቡ፤ በሦስት ቀን ነነዌ ትጠፋለች›› እያለ በከተማዋ አስተማረ:: የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ለጾም ዓዋጅ ነገሩ፤ ሁሉም ማቅ ለበሱ፤ ሦስት ቀን ጾሙ፤ ጸለዩም::

እግዚአብሔርም በሕዝቡ መመለስ ተደሰተ:: ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ:: ቁጣውን በምሕረት መለሰ:: ዮናስ ግን ተቆጣ:: እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይቅርታ ማድረጉ አላስደሰተውም:: ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ:: ‹‹በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህን አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፣ ታጋሽ፣ ምሕረትህም የበዛ አምላክ እንደሆንክ አውቂ ነበርና:: ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ፈጥኜ ነበር:: አሁንም ከሕይወት ሞት ይሻለኛል:: አቤቱ እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ›› አለ::

የዋሁ ነቢይ ዮናስም ደክሞት ተቀመጠ:: ከዚያም እግዚአብሔር ቅል አዘጋጀ:: ቅሉም ለዮናስ ጥላ እንድትሆን ከፍ ከፍ አደረጋት:: ዮናስም ስለ ቅሉ እጅግ ደስ አለው:: በማግሥቱ ግን ቅሉን ትል በላው፤ ደረቀም:: ዮናስንም እስኪዝል ድረስ ፀሐይ ራሱን መታው:: በዚህን ጊዜ ዮናስም ተቆጣ:: እግዚአብሔር ዮናስን ‹‹አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምክባት፣ ላላሳደግሃትም በአንድ ሌሊት ለበቀለች ቅል ካዘንክ እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን ለማያውቁ ከመቶ ሃያ ሺሕ ለሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሳት አላዝንምን?›› አለው::

የዋሁ ነቢይን እግዚአብሔር አምላክ በቅል፣ በትል እና በፀሐይ አማካኝነት ያስተምረውን ትምህርት ተቀብሎ በነነዌ ሰዎች መዳን፣ በእግዚአብሔር መሐሪና ቸርነት ተደስቶ በሰላም ኖረ:: በመስከረም ሃያ አምስት ቀንም የዋሁ ነቢያ ዮናስ በመቶ ሰባ ዓመቱ ሞተ::

ልጆች! እግዚአብሔር መሐሪ፣ ታጋሽ ቸርና ይቅር ባይ ስለሆነ በምሕረቱና በይቅርታው ደስ ይበላችሁ::

ለየዋሁ ነቢይ አምላክ እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤ እኛንም በነቢዩ ጸሎት ይማረን! በረከቱም ከእኛ ጋራ ትኑር ለዘላለሙ፤ አሜን::

*ምንጭ: ትንቢተ ዮናስ፤ መጽሐፈ ስንክሳር ዘወርኃ መስከረም*

# ለመልካም ዕሴቶቻችን ትኩረት እንሰጥ

በረቂቅ መቻል

ክፍል አንድ

በየዘመኑ ልብ ብለን ካስተዋልን ብዙ የሚያስደስቱ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ዓመታት በተፈራረቁ ቁጥር የሚያበሳጩና አግራሞት የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ተመልክተን ወይም ሰምተን ማለፋችን አይቀሬ ነው። አንዳንዴም አስተማሪ የሆኑ ጉዳዮችን ልናይ እንችላለን። ታዲያ በዚህ ዓመት ካስተዋልኳቸው ትዝብቶቼ መካከል አንዱን ለእናንተ ለማካፈል ወደድሁ።

የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ የተፈጠረበትን ዓላማ ዘንግቷል። መልካሙን ከማድረግ፣ የሚጠቅመውንና የሚበጀውን ከመፈጸም በተቃራኒው ከእግዚአብሔር ሕግጋት ርቆ ክፋትን በማመንጨት፣ በተንኮልና በቅናት ተነሣሥቶ በሌላው ላይ ጥፋት ከመፈጸም የተቆጠበበት ጊዜ የለም ማለት ይቻላል። ቃየል ወንድሙን አቤልን በቅናት እንደገደለው ሁሉ አሁን አሁን በሀገራችን አንዱ በአንዱ ላይ በመነሣት ከንብረት ማውደም እስከ ደም ማፍሰስ ድረስ የክፋት መገለጫ የሆኑ ሥራዎች ሲፈጸሙ ማየት የተለመደ ግብር ሆኗል።

ታዲያ እኔም ዕድሜ ለመንገዴ ብዬ አንድ አካባቢ ላይ እየተፈጸመ ያየሁትን ትዝብቴን እነሆ ብያለሁ። ራሳቸውን የበላይ ለማድረግና "የእኔ ብቻ" በሚል አስተሳሰብ ላይ በመመርኮዝ ሌላውን በጠርነት ለማንበርከክ ሲጣደፉና እርስ በእርስ ደም ለማፋሰስ ሲቻኮሉ የታዘብኳቸውን የአካባቢው የጸጥታ ዘርፍ ባለሙያዎችና የማኅበራዊ ድኅረ ገጽ አርበኞችም መመልከት ለኔ የዓመቱ የተለመደ ትዕይንት ነበር።

ዓለማችን የክፉ ሥራ መገለጫ የሆኑ ተግባራት ሲፈራረቁባት ኖራለች። ይህንን የሚደግፉ አካላት ግድያ፣ ዝሙት፣ መዳራት፣ ግብረ ሰዶም፣ ጦርነትና ዝርፊያ፣ .... የመሳሰሉትን ዛሬም ድረስ የሥጋ ግብራቸው እንዲሆን በመትጋት ላይ ናቸው። ታዲያ ውስጤ በጣም ያዝንና እነዚህ ሰዎች ትውልድ እንዲቀጥል አይፈልጉም ማለት ነው እላለሁ። አሁን አሁን በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎችና ግለሰቦች እነዚህ ድርጊቶች ከነውርነት አልፈው በአደባባይ ሲፈጸሙ፣ እንደ ዘመናዊነት እየተቆጠሩም ይገኛሉ።

ከዚህም አልፎ ሰዎች በአንድነት ክፉውንና ደጉን አብረው በመተሳሰብ፣ በፍቅር የኖሩበት ዘመን ተረስቶ አዳዲስ ትርክቶችን በመፍጠር፣ ዘመኑ ያፈራቸውን የጦር መሣሪያዎችና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም የጥፋት እጆቻቸውን ሲሰነዝሩ እንመለከታለን። በቅዱስ መጽሐፍ "ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ" ተብሎ እንደተጻፈ ዓለማችን የፍቅርና የሰላም መገለጫ ከሆኑት መልካም ምግባራት ርቃ የጦርነትና የሽብር ዐውድማ ሆናለች። በዚህም ምክንያት በዘመናችን ዕለት ዕለት እየሰማን ያለነው የጦርነትና ሽብር ወሬ ነው።

አሁን አሁን ለእኔም ሆነ ለሌሎች ወገኖቼ በሀገራችን በኢትዮጵያ በብሔር፣ በሃይማኖትና በዘር በመከፋፈል ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት በአሠቃቂ ሁኔታ ሲጠፋ፣ ለዘመናት ያፈሩት ቤት ንብረት ሲወድም ማየት እየተለመደ መጥቷል። ስጋትና ሽብር፣ ስደትና እንግልት ዘወትር የምንሰማውና የምናየው አሳዛኝ ክስተት ነው። በዚህ ሰዓት ደግሞ በብሔራቸው ወይም በሃይማኖታቸው ምክንያት ሰለባ የሆኑ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ ይገኛል። ይህ ደግሞ ተከባብሮ፣ በፍቅር፣ በሰላም እንዲሁም በጋብቻና በመሳሰሉት ማኅበራዊ ዕሤቶች ለዘመናት ተሳስሮ የኖረ ሕዝብን እንዳይተማመን ከማድረግ አልፎ ለእርስ በእርስ እልቂት የሚዳርግ ነው።

በተለይም ወጣቱ ትውልድ አስተሳሰቡ በአውሮፓውያን መርዛማ የባሕል ወረራ በመመረዙ ቀድሞ ባልነበረ አዳዲስ የታሪክና የማንነት ትርክት ተጠምዶ ክቡር በሆነው የሰው ልጅ ሕይወት ላይ የጥፋት በትሩን በማሳረፍ ሕይወትን እየቀጠፈ፣አካልን እያጎደለ ሀብት ንብረትንም እያወደመ ይገኛል።

ለመነሻ ያህል ከላይ ያነሳኋቸው ዐበይት ትዝብቶቼ ሲሆኑ ወጣቱና የነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ሌሎች

ለግል የፖለቲካ ፍጆታና ለእኩይ ተግባራቸው መፈጸሚያ በቀደዱለት ቦይ ዝም ብሎ መፍሰሱ ሳይ ዝም እንዳልል ተገደድኩ።

ጽንፈኛ የሆኑ አካላት በጎሳና በብሔር፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ ቦይ እየተጓዙ ለዘመናት በበርካታ መልካም ዕሤቶች ተጋምዶ የኖረውን ሕዝብ ለመለያየት ሕዝብን ከሕዝብ እያፋጁ የሴረኞች ዓላማ ማሳኪያ መሣሪያ ሆነዋል ብል ማጋነን አይሆንም። ይህም ሲባል ሴረኞች ወጣቱን በስሜታዊነትና ራሱን መግዛት ባልቻለ አእምሮው ውስጥ መርዛማ የበቀል ጥንስሳቸውን በመጋት የጥፋት ተልእኮአቸው ማስፈጸሚያ እያደረጉት ይገኛሉ። በዚህ ሴራቸውም ውስጥ የእናቶችና የሕፃናት ዋይታና ሰቆቃ፣ የአዛውንቶች እንግልት ሳይገዳቸው የጥፋት ክንዳቸውን እየዘረጉ ናቸው። ውሎ ሳያድር ከዚህ ወደሚከፋ ሀገርን ወደ ሽብርና አለመረጋጋት በመውሰድ ሰዎች እርስ በርስ ከመተባበር ይልቅ ወደ መፈራራት፣ ከመፈራራትም አልፎ ሳይቀድመኝ ልቅደመው ወደሚል አስተሳሰብ ውስጥ በመግባት ምድሪቱን የደም መሬት ለማድረግ ይሽቀዳደማሉ።

# “በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ”

ብዙዎች በተወለዱበትና እትብታቸው በተቀበረበት፣ ክፉና ደጉን ካዩበት ቀዬ መጤ እየተባሉ የመከራ ሰይፍ ሲመዘዝባቸው፣ ቤትና ንብረታቸው የእሳት ሲሳይ ሲሆን፣ ቤተሰብ ሲበተን፣ ሕይወታቸውን ለማትረፍ የድረሱልን ጩኸት ሲጮኹ በዓይናችን ማየቱ፣ በጆሮአችን መስማቱ የዓመቱ ስንክሳር ሆኖ ሳይደረስ የሚቀር አይመስለኝም።

በተለይ አንዳንድ እናቶችና እኅቶች በየቤተ ክርስቲያኑና በየሚዲያ መስኮቱ እንደ ራሔል ዕንባቸውን ወደ ሰማይ እየረጩ ማየቱ የሚያሳዝንና አቤቱ ጌታ ሆይ ወዴት ነው ያለኸው የሚያሰኝ ከሆነ ሰነባብቷል ።

በቅዱስ መጽሐፍ “ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” (መዝ.፷፯፥፴፩) እንዳልተባለች ዛሬ የንጹሓን ደም እንደ ጎርፍ ሲፈስባት፣ በብሔር ፖለቲካ ተተብትባ በተንኮለኞች የተቀበረው የክፋት ፈንጂ ፈንድቶ የብዙዎችን ሕይወት ሲቀጥፍ፣ አካላቸው ሲጎድል፣ ከቀዬአቸው ተፈናቅለው ለስደት፣ ለእንግልትና ለረኀብ በመዳረግ ላይ ናቸው። በዚህም ለጥፋት መሣሪያነት እየዋለ ያለው ወጣቱ ትውልድ ነው።

በጣም የሚሳዝነው ጉዳይ አሁን ያለው ጽንፈኛ ኃይል ሀገር ተረካቢውና ነገ ይህችን ሀገር ይመራል ተብሎ የሚጠበቀው ትውልድ የዚህ ሰለባ ማድረጉ ሳያንስ ወጣቱን ወደ ልማት በማዞር ከድህነት ለመውጣት ከመፍጨርጨር ይልቅ አሁን ላይ ጥፋትን መተዳደሪያው እያደረገ ማየቱ ነው።

“በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ” የሚለውን የቅዱስ መጽሐፍን ምክር ከአእምሮው አውጥቶ በመጣል ጥፋትን እንደ በጎ ተግባር ደጋግሞ በመሥራት ላይ የተሰማራው ይህ አካል ለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሱ በርካታ ችግሮች ቢኖሩበትም በዋናነት ግን ከእግዚአብሔር ሕግጋትና ከመልካም ሥነ ምግባር ማፈንገጥ፣ወጣቱ ትውልድ ዘመናዊነትን በማይገባ መንገድ በመረዳትና በመተግበር ኢትዮጵያዊ ዕሤቶችን በመጣል ራሱን ለአውሮፓውያንና ለመሰሎቻቸው መጤ ባህልና ሴራ ተጋላጭ ያደረገ ይመስላል። በዚህም ቀድሞ የነበረውን እግዚአብሔርን የመፍራትና ክብር ለሚገባቸው ክብርን የመስጠት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ዕሤቶችን አሽቀንጥሮ በመጣል በዘመናዊነት ካባ ሥር ተወሽቆ ለሌሎች እኩይ ተግባር ማስፈጸሚያ ይሆን ዘንድ በሃይማኖት ስምና በብሔር ፖለቲካ በሚነግዱ ቡድኖችና ግለሰቦች እጅ ላይ ወድቋል ቢባል ሐሰት አይደለም።

# ልጅ መውለድ ባለመቻላችን የትዳር ሕይወታችን እየተፈተነ ነው

***ክፍል ሁለት***

ሌላው በአንተ በወንድማችን የሥነ ልቡና ጤናህ ላይ ቀውስ እየፈጠረ ያለው ማሕበራዊ አስተሳሰብን በተሳሳተ መንገድ መረዳትህና የማሕበረሰብ እሴቶችን በአግባቡ ለይቶ አለማወቅ አንዱ ችግር ነው:: ከማኅበረሰብ እሴቶች ሃይማኖት ሲሆን የእኛም ቤተ ክርስቲያን ላለፉት አያሌ ዓመታት ምእመኖቿ በትዳርና በሌሎች ጉዳዮች ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ የምትሰጥባቸውና የምታስተምርባቸው መድረኮች ብዙ ናቸው:: ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በትዳር ሕይወታቸው ላይ የሚያጋጥሙቸውን ችግሮች ወደ ሃይማኖት አባቶች ከማምጣት ይልቅ በቅርብ ባሉ የማኅበረሰብ ሽማግሌዎች በመሄድ ለችግራቸው መፍትሔ ይፈልጋሉ:: ይሁን እንጂ ቅድስት ቤተ ክርቲያን በየ ደረጃቸው ለሚመጡ የትዳርና የቤተሰብ ጉዳዮች መፍትሔ አላት :: ይህንን ካለማወቅ ብዙ ሰዎች ችግሩ ሥር ከሰደደ በኋላና አማራጭ ሲያጡ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የመጨረሻ አማራጭ አድርገው በመውሰድ ጉዳያቸውን ምሥጢራዊ በሆነ መልኩ ለካህንም ሳይናገሩ ወደ እግዚአብሔር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ጥያቄያቸውን ሲገልጹ ይታያል:: ለምሳሌ የጨነቃቸውን ነገር በሀዘን፣ ስዕለት በማድረግ (ቃል) ለእግዚአብሔር በመግባት እንዲህ ብታደርግልኝ ፤ ይህንን ችግሬን ብትፈታልኝ ይሔንን ይዤ እመጣለሁ ወ.ዘተ በማለት ይሳላሉ::

ውድ ጠያቂያችን ይህ አይነቱ አካሔድ የአንተ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ባለትዳሮች ሕይወት ውስጥ እንደምንሰማው ትዳራቸው በተፈቀደው መንፈሳዊ መንገድ አለመቃኘቱ ብሎም ከቤተ ክርስቲያን አስተምሮ ውጭ በሆነ መንገድ መመስረቱ ትዳራቸውን ያለጊዜው እንዲፈርስ ያለ ዓላማ እንዲኖሩ ሆነዋል:: ይሁንና አንተ በልጅነት እድሜህ በቃለ እግዚአብሔር ተኮትኩተህ አድገህ አሁን በተለያየ የዓለም ወጥመድ ከእግዚአብሔር እቅፍ የወጣህ ቢመስልህም እንዳትሳሳት:: የቀደመው ጥቂት የክርስትናህ እርሾ ብዙ ይሰራልና በትዕግስት ነገሮችን ልታይ ያስፈልጋል:: ዋናው ጉዳይ ልጅ መውለድ አለመውለድ አልያም በሩካቤ አለመጣጣም አይደለም ቁልፍ ተግባሩ:: እግዚአብሔር በናንተ ሕይወት ውስጥ ይሄንን ለምን አደረገ ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ አሮጊቷ ሳራ ሽማግሌው አብርሐምም እድሜያቸው ካለፈ በኋላ ልጅ ወልደዋል :: በእግዚአብሔር ተጎብኝተዋል ፈጣሪ ልጅ እንዳይኖር የፈለገበትን ዓላማን በማስተዋል በመገንዘብ በጸሎትና በትዕግስት በመጠበቅ አስተውሎ ማየት ያስፈልጋል:: በጥድፊያ እግዚአብሔርን ወደ ሚያሳዝን ውሳኔ መግባት፣ፍቺንና ከትዳር ውጪ ደስታን ፍለጋ አለመሔድህ በእምነት መጽናት ያስፈልጋል:: አንተም ሆንክ ባለቤትህ ሰዋዊ ፍላጎታችሁን አምቃችሁ በትዕግስት፣በጸሎትና በመበረታት ከእግዚአብሔር የሚሆነውን እስከ መጨረሻው ልትጠብቁ ይገባል::

ውድ ጠያቂያችን በአንድም በሌላ መፍትሔ የሚሰጠው እግዚአብሔር ነውና ከላይ የተጠቀሱት መፍትሔዎች እንዳሉ ሆነው በመንፈሳዊ ሕይወታችን ልንጠቀምባቸው የሚገቡ መፍትሔዎች የሚከተሉት ናቸው::

## ጸሎት

በትዳር ሕይወት ውስጥ በሩካቤ ሥጋ ያለመጣጣም ችግርን ምክንያት አድርጎ ትዳርን ለመበተን ወይም ሰላምን ለማሳጣት የሚተጋውን ዲያብሎስን ከምናርቅበት መንገዶች አንዱ ጸሎት ነው:: በመሆኑም ጸሎት ባልና ሚስት በትዳራቸው ማግኘት ያለባቸውን ደስታ እንዳያገኙ በመሃል እየገባ እንዳይስማሙ፣ እርስ በርስ እንዲጠራጠሩ፣ የሚያደርጋቸውን ጠላት ዲያብሎስ የሚያሸንፉበት መሣሪያቸው ነው::

በመጽሐፈ ጦቢት ተጽፎ እንደምናነበው የራጉኤል ልጅ ሣራ ለሰባት ወንዶች አጋብተዋት አስማንድዮስ የሚባል ክፉ ጋኔን ከጭኗ ላይ አርፎባት ሰባቱን ባሎቿ እንዲሞቱ አድርጓቸዋል። ኋላም ጦብያን አጋቧት። “ወደ ጫጉላቸው ባስገቧቸው ጊዜ ጦብያ ከአልጋው ተነሥቶ፡- “እኅቴ ተነሽ፥ እግዚአብሔር ይቅር ይለን ዘንድ እንጸልይ” አላት። ከዚያም “አቤቱ የአባቶቻችን አምላክ አንተ ቡሩክ ነህ፤ ቅዱስ ስምህም ይባረክ፤ ለዘለዓለሙም ይመሰገናል። ሰማያትና የፈጠርሃቸው ሁሉ ያመሰግኑሃል። አንተ አባታችን አዳምን ፈጠርኸው፤ ትረዳውና ታሳርፈውም ዘንድ ሔዋንን ሰጠኸው፤ ከእነዚያም የሰው ዘር ተወለደ፤ አንተም አልህ፡- ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለምና የሚረዳውን እንፍጠርለት። አሁንም ይህቺን እኅቴን የማገባት በሚገባ ነው እንጂ ስለ ዝሙት አይደለምና አቤቱ አብረን ወደ ሽምግልና እንድንደርስ እንረዳዳ ዘንድ ለእኔና ለእርሷ ይቅርታን ላክልን።” በማለት ሲጸልይ ሣራም ከእርሱ ጋር “አሜን” እያለች በጸሎቱ እንደተባበረች ተጽፏል። ከጸሎታቸውም በኋላ ሁለቱም በዚያች ሌሊት አብረው አደሩ። ከጸሎታቸውም የተነሣ ጋኔኑ ከሣራ መራቁን እንረዳለን። (መጽሐፈ ጦቢት. ፰፥፬-፱ ፣ ፫፥፯-፱) በመዝሙረ ዳዊት “ጻድቃን በክብሩ ይመካሉ፤ በመኝታቸውም ላይ ሐሤትን ያደርጋሉ።” ተብሎ እንደተጻፈ ባልና ሚስት ሩካቤ ሥጋ የተሰጠበትን ዓላማ በአግባቡ እንዲፈጽሙ እንዲሁም ጣዕምና ደስታ ያገኙበት ዘንድ መጸለይ ይገባቸዋል። (መዝ. ፻፵፱፥፭)

በገድለ አቡነ ሀብተ ማርያም ከተጠቀሱት ተአምራት አንዱ ፈቃደ ሥጋውን መፈጸም ስላልቻለ ሰው ይናገራል። ይህ ሰው ፈቃዱን በአግባቡ መወጣት ባለመቻሉ ወደ ጻድቁ ገዳም በመሔድ ችግሩ ይወገድለት ዘንድ ጸልዮ ሲመለስ የነበረበት ችግር እንደራቀለትና በትዳሩ ተደስቶ እንደኖረ ተጽፏል። በመሆኑም ፈቃደ ሥጋቸውን በአግባቡ መፈጸም ያልቻሉ ሰዎች ጸሎት በማድረግ ፈጣሪያቸውን መማጸን ከቅዱሳን ርዳታን መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

ስለዚህ የተቀደሰው ሩካቤ ሥጋና የተባረከ ልጅ በፈቃደ እግዚአብሔር ስለተሰጠ የተሰጠበትን ዓላማ እንዳይስት በሥርዓት ይፈጸምና በአግባቡ የሚፈለገውን ደስታ ያስገኝ ዘንድ መጸለይ የሚገባ ሲሆን ይልቁንም ባልና ሚስት ፈቃዳቸውን ለመፈጸም የማያስችል እክል ሲገጥማቸው ደግሞ በይበልጥ በጸሎት በመትጋት ፈጣሪያቸው ፈተናቸውን እንዲያርቅላቸው፣ ቅዱሳኑ ደግሞ እንዲራዷቸው መትጋት ይኖርባቸዋል።

## መረዳዳት

የሰው ልጆች ከእነርሱ ዕውቀት፣ አቅምና ጉልበት በላይ ለሆኑ ነገሮች ረዳት ያስፈልጋቸዋል። አንዱ ያለው ሌላው የለውም፤ ሌላው ያለው ደግሞ አንዱ የለውም። በመሆኑም ባልና ሚስት የተቀደሰውን ጋብቻ መሥርተው በሚኖሩት የትዳር ሕይወት ውስጥ ከሚያገኟቸው ጥቅሞች አንዱ አንዳቸው የአንዳቸውን እርዳታ ማግኘታቸው ነው።

የባል ፍጹም ረዳቱ ሚስቱ ናት፤ የሚስት ፍጹም ረዳቷ ባሏ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ሔዋንን ለአዳም ሲፈጥር “ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚረዳውን ጓደኛ እንፍጠርለት እንጂ” ያለው ይህን ያስገነዝባል። (ዘፍ. ፪፥፲፰)

በተመሳሳይ ቅዱስ ጴጥሮስ “እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ፥ ከሚስቶቻችሁ ጋር ስትኖሩ፥ ሚስቶቻችሁን አክብሩ፥ እነርሱ ከእናንተ ጋር ክብርንና ሕይወት ይወርሳሉና።” በማለት ሚስቶች “ተፈጥሮአቸው ደካማ ነውና” በማለት በባሎቻቸው መረዳት የሚገባቸው መሆኑን ተናግሯል። (፩ጴጥ. ፫ ፥፯-፱)

በመሆኑም ባልና ሚስት በኑሯቸው የሚገጥማቸውን ውጣ ውረድ ለመግፋት ከሚያደርጉት መረዳዳት በተጨማሪ በሐሳብ እንዲሁም በስሜት በረቀቀ መልኩ ይረዳዳሉ። ከተረዳዱም የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲያገኙ ፈጣሪ ይረዳቸዋል። ስለዚህ አንተም ሆንክ ባለቤትህ በአግባቡ ፈቃደ ሥጋውን መፈጸም ያልቻለውን ሰው ያለበትን ችግር በመረዳትና በመንፈሳዊውም ሆነ በሕክምና ጥበብ የሚረዳበትን መንገድ በማመቻቸት መተጋገዝ ይገባል እንጂ ጸብና ክርክርን በማስቀደም ለመለያየት መንገድ መጥረግ አይገባም።

## የጋብቻ ዓላማ ጊዜያዊ ደስታ አለመሆኑን መረዳት

በቅዱስ ጋብቻ የሚወሰኑ ጥንዶች ዓላማቸው አካላዊና ጊዜያዊ ደስታ ላይ ያተኮረ አይደለም:: እያንዳንዱ የትዳር አጋር ሌላውን/ሌላዋን ሰው በመሆኑ/በመሆኗ ለተጣማሪያቸው ንጹሕ ፍቅርን ከርኅራኄ ጋር መስጠት አለባቸው፤ ይህም ሲባል የተጣማሪውን አእምሮ ደኅንነት፣ ምግባር፣ ፀባይ፣ መላ አካልን ተቀብሎ መኖርን ይጠይቃል:: ሩካቤ ሥጋ ደግሞ ጥልቅ የሆነውን ውስጣዊ ፍቅርን መግለጫና ማረጋገጫ መንገድ ቢሆንም በተራክቦ ሥጋ ብቻ ደግሞ እውነተኛ እርካታ አይገኝም:: ሆኖም የውስጥ ስሜትንና ጭንቀትን እንዲቀንስ ግን ያደርጋል:: ያ ደግሞ ጊዜያዊ ደስታን ያመጣል እንጂ ዘላቂ አይደለም::

በመሆኑም በቅዱስ ጋብቻ የተመሠረተ ትዳር ንጹሕ ስሜትንና የጋራ መንፈሳዊ ሕይወትን ገንዘብ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን ምሉዕ የሆነ ደስታን መጎናጸፍን ዓለማው ያደረገ ነው:: ስለዚህ በተጋቢዎች መካከል ሊኖረው የሚገባውና ጊዜያዊ ደስታን የሚያስገኘው ሩካቤ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከጥንዶቹ ባንዳቸው ሊፈጸም ባይቻል ዘላቂ የሆነውን ዘለዓለማዊ ደስታ በማሰብ በፍቅር ሊታገሡት ይገባል::

## አንዳቸው ሌላቸውን ማበረታታት

ምንም እንኳ በተቃራኒው ወገን ሩካቤን ለመፈጸም ድክመት፣ ልጅ አለመውለድ ችግር ቢኖርም አጋርን ከነችግሩ በመቀበል በሩካቤ ጊዜ በሚያደርገው ጥረት መደገፍና እርካታን መግለጥ ይገባል:: ይህ ደግሞ ጥንዶቹን ባላቸው ነገር አመስጋኝና ደስተኛ እንዲሆኑ፣ የሚያልፈውን ደስታ በማሰብ የአጋራቸውን ሕሊና ከሚነኩ ንግግሮች ወይም ድርጊቶች እንዲታቀቡ፣ አጋራቸው በጊዜ ሒደት ካለበት ችግር እንዲወጣ እንዲያግዙ እንዲሁም ትዳርን ከመፍረስ እንዲጠብቁ ይረዳቸዋል::

## የንስሐ አባትን ማማከር

ክርስቲያን ሕይወቱን በምክረ ካህን መምራት ይጠበቅበታል:: የንስሀ አባቶች የንስሀ ልጆቻቸውን የወደፊት ሕይወት አቅጣጫ የማስያዝ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ድልድይ ሆነው የማገናኘት፣ የንስሐ ልጆች ጋር በሀዘን በደስታ ተገኝተው መንፈሳዊ አገልግሎት የመስጠት እና በዕለት ዕለት ለሚያጋጥሟቸው ፈተናዎችን ሊመክሩ ሊያጸኑ ብሎም ለእኛ የተሰጡን እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው:: ስለዚህ ለንስሐ አባቶች የትኛውንም አይነት ችግር ቢገጥመን ሳንደብቅ፣ ሳንፈራ፣ ሳናፍር፣ ችግራችንን በመናገር በምክራቸው በጸሎታቸው ሊራዱን ስለሚችሉ በግልጽ ከንስሐ አባት ጋር በመመካከር ለችግራችን በወቅቱ መፍትሔ ልንፈልግ ያስፈልጋል:: ውድ ጠያቂያችን አንተም የንስሀ አባት ከሌለህ የንስሀ አባት በአጥቢያህ የሚያገለግሉ አባቶችን በመያዝ አሁን ያለብህን ከባድ ፈተና ለሰውና ለባልንጀራ ከማማከር ከንስሐ አባታችሁ ጋር በመሆን ሳትፈሩ በግልጽ በመወያየት ወደ መፍትሔ ልትመጡ ይገባል::

ውድ ጠያቂያችን በአጠቃላይ ያጋጠመህ የትዳር ሕይወት ችግር ከመንፈሳዊ ዕውቀት ማነስ ብሎም ለሀይማኖታዊ ጉዳዮች ትኩረት ካለመስጠትና ትዳርን በጥበብ ካለመምራት የተነሣ ነው:: ስለዚህ ምህረቱ የበዛ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ስለሚችል አሁን ካላችሁበት ከተሳሳተ የትዳር አካሄድ ለመውጣት በመወሰን በንስሀና በልብ ዝግጅት እንድታደርጉ ብሎም በሩካቤ፣ በልጅ አጦት ሳቢያ ደስታ ማጣት፣ ችግሩን መፍትሔ እንደሌለው አድርጎ ማሰብ፣ ይሉኝታና ማህበራዊ መገለልን መፍራትን ማቆም ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለባችሁ:: ይህ እንዳለ ሆኖ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ጋብቻ ቅዱስ መኝታውም ንጹሕ ነውና ስለ ሩካቤ ሥጋ በግልጽ በጨዋነት ማውራት መመካከር የሚያሳፍር ነውር ስላልሆነ መመካከራችሁ ሊቀጥል ይገባል:: የልብ መዘጋጀት ከሰው ፣ የነፍስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር እንደሚባለው መልካም ሀሳቦችን ይዛችሁ ፈጣሪን ከተማጸናችሁ የለመኑትን የማይነሳ መድኃኔዓለም በትዳራችሁ የጎደለውን ሁሉ ይሞላል::